# የንባብ ልምድና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፡- በወቅሮ፣ በነጋሽና አጉላዕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናሙናነት

በ


ብርሃን ስራጅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለተግባራዊ
ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.
ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


መጋቢት 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ**
**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል**
**ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

# የንባብ ልምድና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፡- በወቅሮ፣ በነጋሽና አጉላዕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናሙናነት

በ

**ብርሃን ስራጅ**

የፈተና ቦርድ አባላት

______________ 22/07/03 ______________

አማካሪ ቀን ፊርማ

______________ 22/07/03 ______________

ፈታኝ ቀን ፊርማ

መጋቢት 2003 ዓ.ም

# ምስጋና

ከርዕስ መረጣው ጀምሮ ቅን ትብብራቸው ሳልተለየኝ፣ በኃላም ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጥናቱን በጥልቀት በመመርመር ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠትና ጽሑፉን በወቅቱ በማራምና ትክክለኛ ቅርጽ በማስያዝ ከፍፃሜ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለረዳት ኘሮፌሰር ጌታቸው እንዳላማው የማቀርበው ምስጋና ላቅ ያለ ነው፤፡

በዚህ የትምህርት ዕድል እንድጠቀም የፈቀደልኝንና የሁለት ዓመት ሙሉ ደመወዝ በመክፈል ያስተማረኝን የውቅሮ ወረዳ፣ እንዲሁም ለዚህ ጥናት ማከናወኛ የሚሆን በጀት በመስጠት የተባበረኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ትምህርቴን በሚገባ እንድከታተልና ጥናታዊ ጽሑፌን በሚገባ እንድሰራ በትዕግስት ከጎኔ ለቆሙት ባለቤቴ አቶ መሐመድ ኑር፣ልጆቼ፣ ባልደረባዬ ዓወት ከድር እንዲሁም ይህን የጥናት ሥራዬን በማንበብና አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ የክፍል ጓደኞቼና በስታስቲክስ ስራ ለተባበሩኝ አቶ አብርሃ አስፋው ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው ፡፡

በመጨረሻም በአጭር ጊዜ ውስጥ የጥናቱን ጽሑፍ በኮምፒዩተር በመተየብ ከመልካም ስነ-ምግባር ጋር ጽሑፉን ሳጠናቀቀችልኝ አርማዬ አደራን ምስጋናዬ ይድረሳት፡፡

# ማውጫ

ገጽ


ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ iv
የአባሪ ማውጫ ........ v
አጠቃሎ ........ vi

**ምዕራፍ አንድ**
**መግቢያ**
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. አነሳሽ ችግሮች ........ 3
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 4
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7 ያጋጠሙ ችግሮች ........ 5
1.8 የቃላትና የሐረጋት መፍቻ ........ 5

**ምዕራፍ ሁለት**
**ክለሳ ድርሳናት**
የንባብ ልምድ ........ 6
2.1 የንባብ ልምድ ምንነት ........ 6
2.2 በንባብ ልምድ ላይ ያሉ ተጽእኖዎች ........ 8
2.3. የንባብ ልምድ ማጐልበቻ መንገዶች ........ 9
2.3.1. በትምህርት ቤት ውስጥ የንባብ ልምድን ማጎልበት ........ 9
2.3.2. ከትምህርት ቤት ውጭ የንባብ ልምድን ማጎልበት ........ 11
2.3.3. በንባብ ጊዜ ጠቃሚ ዘዴዎችን በአግባቡ መጠቀም ........ 13
2.4 የአንባቢያን ዓይነቶች ........ 13
2.4.1 ብቁ የሆኑ አንባቢያን ........ 13
2.4.2 ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ........ 14
2.5. ብቁ የሆኑና ያልሆኑ አንባብያን አበይት ባህሪያት ........ 15
2.5.1. ብቁ የሆኑ የአንባብያን ባህሪያት ........ 15
2.5.2 ብቁ ያልሆኑ የአንባብያን ባህሪያት ........ 16
2.6. አንብቦ መረዳት ........ 17
2.6.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት ........ 17

2.6.2. የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች .................... 18
2.6.2.1. የቃላትና ሀረጎችን ፍች መረዳት .................... 18
2.6.2.2. የጽሑፍን ግልጽ መልዕክት መገንዘብ .................... 18
2.6.2.3. የጽሑፉን ውስጣዊ መልዕክት መገንዘብ .................... 19
2.6.2.4. የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ ሃሳብ ፍሰት መገንዘብ .................... 19
2.6.2.5. የአያያዦችን ሰዋስዋዊ አገባብና ትርጉም መረዳት .................... 19
2.7. የንባብ ስልቶች .................... 20
2.7.1. የፍጥነት ንባብ .................... 20
2.7.2. የአሰሳ ንባብ .................... 20
2.7.3. ጥልቅ ንባብ .................... 21
2.8 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ .................... 21
2.9 በሀገር ውስጥ የተደረጉ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት .................... 23

ምዕራፍ ሶስት
የአጠናን ዘዴ .................... 26
3.1 የናሙና አመራረጥ .................... 26
3.1.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ .................... 26
3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ .................... 26
3.1.3 የተጠኚዎች አመራረጥ .................... 27
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች .................... 27
3.2.1 የጽሑፍ ፈተና .................... 27
3.2.2 የጽሑፍ መጠይቅ .................... 28
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ .................... 28

ምዕራፍ አራት
የመረጃ አቀራረብ ትንተናና ማብራሪያ .................... 30
4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና .................... 30
4.1.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና .................... 30
4.1.2 ከክፍል ሁለት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና .................... 39
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ .................... 42

ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች .................... 47
5.1 ማጠቃለያ .................... 47
5.2 የመፍትሔ ሃሳብ .................... 49
ዋቢ መፅሃፍች .................... 51
አባሪዎች

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሰንጠረዥ 1. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ ---------------------------------------- 22
ሰንጠረዥ 2. በየትምህርት ቤቱ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ ተማሪዎችን ብዛት የሚያሳይ መረጃ ........................................ 30
ሰንጠረዥ 3. በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ የተገኙ መረጃዎች.................... 31
ሠንጠረዥ 4. በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ለማጎልበት በመምህራን የሚደረገውን እገዛ በተማሪዎች እይታ ------------------- 32
ሰንጠረዥ 5. ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ ያላቸው የንባብ ልምድ ------------- 34
ሰንጠረዥ 6. የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ........................................ 35
ሰንጠረዥ 7. ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚያሳዩአቸውን ባህሪያት.................. 37
ሠንጠረዥ 8. የማንበብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች ከቤተ መጻሕፍት ጋር ያላቸውን ቁርኝት አስመለክቶ የተገኙ መረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ ---------------------------------------- 39
ሰንጠረዥ 9. የተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ችሎታ በተግባር የማዋል ብቃት ለመገምገም ከተሰጡት ፈተና የተገኙ መረጃዎችን የሚያመለክት ሰንጠረዥ ---------------------------------------- 40
ሰንጠረዥ 10. የተማሪዎች የንባብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ ...41

# የአባሪ ማውጫ


አባሪ 1. በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ------------------------------------------------------------- 55
አባሪ 2. በተማሪዎች የሚሰራ ፈተና ------------------------------------------------------------- 59
አባሪ 3. የተማሪዎች የንብብ ልምድና የአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት
ችሎታ መደበኛ ልይይት ------------------------------------------------------------- 67
አባሪ 4. የተማሪዎች የንብብ ልምድና የአማርኛ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ ስሌት -- 68
አባሪ 5. ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ችሎታና ችሎታቸውን በተግባር ለማዋል
ያላቸውን ብቃት ለመፈተህ በተሰጠው ፈተናተማሪዎቹ ያገኙት ውጤት
በመቶኛ------------------------------------------------------------- 72
አባሪ 6. የቀረበው ፈተናአስተማማኝነት------------------------------------------------------------- 73
አባሪ 7. የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታና ችሎታቸው በተግባር የማዋል
ብቃት ለመፈተሽ የቀረበው ፈተናጥያቄዎች የአስቸጋሪነት መጠን ----------- 74

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አላማ በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነበር። አላማው ከግቡ እንዲደርስ በ2003 ዓ.ም በውቅሮ ፣ በነጋሽና በአጉላዕ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ10ኛ ክፍል ከሚማሩ 1880 ተማሪዎች 5% በመውሰድ በአጠቃላይ 94 ተማሪዎች በተራ የናሙና አመራረጥ ስልት (Random Sampling Method) አማካኝነት በተጠኚነት ተመርጠዋል። የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሑፍ መጠይቅና የጽሑፍ ፈተና ነበር። ይህ ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ከግብ ለማድረስ ከአይነታዊ የምርምር ስልት እና በከፊል መጠናዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም ነበር። የመረጃ መተንተኛዎቹም መቶኛ፣ መደበኛ ልይይት፣ የተዛማጅ ስሌትና የአስተማማኝነት ግንኙነት መለኪያ ስልቶች ነበሩ። ከተገኘው የመረጃ ትንታኔም የተማሪዎች የማንበብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሌላቸው ውጤቱ አመልክቷል። ከዚህ በመነሳትም በተማሪዎች የንባብ ልምድና የአማርኛ አንብቦ በመረዳት ችሎታ ውጤት መካከል ያለው ዝምድና አዎንታዊ ነው። ይህም ውጤት የንባብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት ውጤት ያስመዘግባሉ፤ በአንጻሩ የንባብ ልምድ የሌላቸው ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት የሚያስመዘግቡት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑን አሳይቷል። ለአሉታዊ ውጤት መመዝገብ ተጠቃሽ ከሚሆኑ ምክንያቶች መካከል ጊዜ ማጣት፣ ወላጆቻቸው አስፈላጊ የሆኑ መጻሕፍትን ለልጆቻቸው አለማቅረባቸው፣ መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በቂ መለማመጃዎችን በማቅረብ እገዛ አለማድረጋቸው የሚሉት ይገኙበታል። በነዚህ መነሻነትም የተማሪዎችን የንብብ ልምድ ለማሳደግ የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ተከታትለው አመርቂ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የተለያዩ ችሎታዎችንና ልምዶችን በሂደት ማጎልበት ይኖርባቸዋል። ከነዚህም ውስጥ ጥሩ የንባብ ልምድን ማዳበር አንዱና ዋነኛው ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት በአብዛኛው ሰፊ ጊዜ ወስዶ ማንበብን የሚጠይቅ ነው። ሆኖም Farrant (1977:30) እንደገለፁት ተማሪዎች ትምህርታቸውን አዘውትረው የሚያጠኑት በማንበብ ቢሆንም ብዙዎቹ በቂ የንባብ ልምድን ቀድመው ስለማያዳብሩ ችግር ሲገጥማቸው ይታያል። Graham (1967:78) በበኩላቸው "ጥሩ የንባብ ልምድ ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ትምህርትን ለመቀጠል መሠረታዊ ነገር መሆኑ አጠያያቂነት የለውም" ይላሉ። ይህም የሚያስገነዝበው ተማሪዎቹ በትክክለኛ የማንበብ ስልት የታገዘ ጥሩ የንባብ ልምድ ካላጎለበቱ በክፍል የሚጽፏቸውን ማስታወሻዎችም ሆነ የተለያዩ መፃሕፍትን አንብበው በመረዳት የሚቀርብላቸውን ንባብ በአግባቡ ለመረዳት እንደሚቸገሩ ነው።

Conley (1992፤67) በበኩላቸው እንደገለፁት የተማሪዎች የንባብ ልምድ ጥሩ መሆኑንና አለመሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ በትምህርታቸው ውጤት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። ይህ በንባብ ልምድና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ትስስር ሊኖር እንደሚችል ይጠቁማል። ከዚህም ሌላ Nelson (1984:2) "የማንበብ ክሂልና ልምድ ትምህርታቸውን ለሚያጠኑ ወይም ማጥናት ለሚያቅዱ ተማሪዎች ከሌሎች ክሂሎች በበለጠ ያስፈልጋቸዋል" ይላሉ። ይህም አገላለፅ የንባብ ልምድን አስፈላጊነት ይበልጥ ያጎላዋል።

Arcy (1973:3) እንዳብራሩት ደግሞ ተማሪዎች በቂ የንባብ ልምድ ከሌላቸው የማንበብ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፤ በመሆኑም አንድን ፅሁፍ ማንበብ ጀምረው ከመጨረስ ይልቅ በመሃል አቋርጠው የመተው ባህሪ አዘውትሮ ይታይባቸዋል። እንዲሁም Conley (1992) እንደገለፁት የተማሪዎች የንባብ ልምድ ደካማ ከሆነ የሚማሩትን ትምህርት በራሳቸው የመገምገም ብቃታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፤ ይህም

በግላቸው እያነበቡ እውቀታቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉትን ጥረት ሁሉ ያደናቅፉዋል፡፡

ጥሩ የንባብ ልምድን አዳብሮ መገኘት ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ከክፍል ወደ ክፍል ለማሸጋገር እገዛ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ አለው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በርካታ የእውቀት ክምችት የሆኑ የጥናት ውጤቶች ሰፍረው የሚገኙት በፅሁፍ ነውና፡፡ በመሆኑም ትክክለኛ የንባብ ልምድ አዳብሮ ከመገኘት ውጭ ከእነዚህ ክምችቶች ተጠቃሚ ለመሆን አይቻልም (Huyland 1990፡87) ፡፡

የንባብ ልምድ በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ የተለያዩ ምሁራን ተገልጿል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ጌታቸው (1986) የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱን ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ አለማየሁ (1986) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ ይዘት ባላቸው ምንባቦች በመጠቀም ንባብን ከፅህፈት ክሂል በማዛመድ ማለማመድ የተሻለ ውጤት እንደሚያገኝ ያመለክታሉ፡፡

የማስተዋል (1989፡49) የጽሑፍ ሥራ ደግሞ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ባካሄዱት ጥናት የተማሪዎቹ ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ችግሩ በአማርኛ አፋቸውን በፈቱትም ሆኑ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩት ተማሪዎች ውጤት ላይ በግልፅ መታየቱን ጠቁመዋል፡፡ እንዲሁም ሰለሞን (1990፡3) የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጠናከር የሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተግባር ያለመዋላቸውን፣ በዚህም የተነሳ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና ባጠቃላይም የንባብ ባህልን ለማዳበር ልዩ ልዩ ስልቶችን አለመቀየሳቸውን ይጠቁማሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ይህንን አስፈላጊና ጠቃሚ ችሎታ ለማዳበር ያለው አጠቃላይ ጥረት በአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ላይ ምን ይመስላል? ብለን ብንጠይቅ ክሂሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን አንብቦ የመረዳት ችሎታን የፈተሹ አጥኚዎች ጌታቸው (1986)፣ በድሉ (1988)፣ ግርማ (1988)፣ ተስፋዬ (1986)፣ አጥናፉ (1988)፣ ማስተዋል (1988)፣ የኔሰው (1990) ያመለክታሉ፡፡ ለተማሪዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን ጌታቸው (1986) እና ተስፋዬ (1986) በጥናታቸው እንዳመለከቱት ምክንያቱ የንባብ ልምድ ማነስ ሲሆን ሌሎቹ በምክንያትነት የሚጠቅሱት የትምህርት አሰጣጡ ችግር መኖሩን ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው አጥኚዋ ያገኘቻቸውን በማንበብ ክሂል ዙርያ የተደረጉ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም በተማሪዎች የንባብ ልምድና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ትስስር በቀጥታ አልተመለከቱትም፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና አነሳሽ ችግር/ምክንያት ዝምድናቸው ምን እንደሚመስል ለመጠናቱ ነው።

## 1.2 አነሳሽ ችግሮች

አጥኚዋ በውቅሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባስተማረችበት የተወሰኑ አመታት በአስረኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በየአመቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስመዘግቡት ዝቅተኛ ውጤት ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ በማስነሳት በአንብቦ መረዳት ችሎታና በንባብ ልምድ መካከል ያለውን ዝምድና ማጥናት ችግሩንና የችግሩ መፍትሔ ያሳያል የሚል የጸና እምነት በአጥኚዋ በኩል መፈጠሩ ነው፡፡

ሌላው ችግርም በንባብ ክሂል ዙሪያ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል በተማሪዎች የንባብ ልምድና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ዝምድና ግን ከዚህ በፊት የተጠና ጥናት የለም፡፡

በመሆኑም በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል በጥናት ማረጋገጥ ለመማር ማስተማር ስራ አንዱ ተገቢና አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ አጥኚዋ ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳስታለች። በመሆኑም የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥናቱ መልስ ያገኛሉ።

1. በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ግንኙነት አለ ወይስ የለም?
2. ለተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ መሆንና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማነስ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?
3. ዝቅተኛ የንባብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች አስተማሪዎች ማድረግ ያለባቸው ነገር ምንድነው?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የንባብ ልምድን ለአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ችሎታ ያለው ተዛምዶ ለመፈተሽ ነው፡፡

ጥናቱ ከዋናው ዓላማ በመነሳት የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይሞክራል፡፡

1) የተማሪዎችን የንባብ ልምድ በመዳሰስ በንባብ ልምዳቸውና በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መካከል ያለውን ዝምድና በንፅፅር ማሳየት፡፡
2) የተማሪዎቹ መሠረታዊ ችግርና የችግሩ መንስኤ ምን እንደሆ ለመለየት መሞከር

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፣

1) የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸውን ለማሻሻል መምህራን ምን እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ ይጠቁማል፣
2) የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች በግላቸው ልምዳቸውን እንዴት ማሻሻል እንደሚችሉ ዘዴዎችን ይጠቁማል፣
3) በሌሎች የትምህርት ዓይነቶችና በተማሪዎች የንባብ ልምድ መካከል ያለውን ግንኙነት በሰፊው ማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች መነሻ ይሆናል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ዝምድና በመመርመር ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ጥናቱ የንባብ ልምድ ለአንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው ተዛምዶ በሙከራ የማረጋገጥ ዓላማ የለውም፡፡ ጥናቱ የተማሪዎች የንባብ ልምድ ምን እንደሚመስል ጥንካሬያቸውና ድክመታቸውን ከመገምገም አልፎ ለአንብቦ መረዳት ክሂል ትምህርት የቀረቡ ይዘቶችን፣ ክንውኖችን (መልመጃዎችን) ከትግበራ ቴክኒክ አኳያ የሚኖሯቸውን ሚናዎች እንዲሁም ለቀረቡበት የክፍል ደረጃ ተገቢነታቸውን የሚመዝንና የሚገመግም ጥናት አይደለም፡፡

ጥናቱ በተተኳሪ ትምህርት ቤትና የክፍል ደረጃም ውስንነት ይታይበታል፡፡ ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሁለተኛ ቋንቋነት ከሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በውቅሮ፣ በአጉላዕና በነጋሽ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በናሙናነት በመውሰድ የንባብ ልምድ ለአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለውን ተዛምዶ ብቻ ይፈትሻል።

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት ሲካሄድ የተወሰኑ ችግሮች አጋጥመዋል፡፡ መጠይቁን ለማሰራጨትና ለመሰብሰብ የትምህርትቤቶቹ ቦታ አቀማመጥ የተለያዩ በመሆናቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞኛል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ረዳት ሰዎችን በፈለግና በመጠየቅ የመጠይቁን ዓላማ ከገለጽኩና ሐሳቤን ካስረዳኋቸው በኋላ ለማሰራጨትና ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ሌላው ችግር የንባብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ዝምድና በስታስቲክስ አማካይነት ለመስራት አስቸግሮኝ ነበር፡፡ ይህንንም ሁኔታ ለማሳካት ያመች ዘንድ የባለሙያ ማፈላለግ ሂደት በማካሄድ የዝምድናውን ውጤት ለማግኘት ችያለሁ፡፡

## 1.8 የቃላትና የሐረጋት መፍቻ

- ስነ-መዋቅራዊ ጥቆማ፡- ቃላት በዐ/ነገር ውስጥ ያላቸውን የአወቃቀር ቅደም ተከተል ወይም ክፍላቸውን መሰረት በማድረግ ፍቻቸውን እንዲታወቅ ማድረጊያ፣
- ስነ-ድምፃዊ ጥቆማ፡- በቃላት ውስጥ የሚገኙ ድምፆቹን ዝምድናና ሁኔታ መሰረት በማድረግ ፍቺ እንዲታወቅ ማድረጊያ፣
- ዳራዊ ጥቆማ፡- ያለፈውን የህይወት ልምድና ገጠመኝ መሰረት በማድረግ ፍቺ እንዲታወቅ ማድረጊያ፣
- ባህላዊ ጥቆማ፡- የቋንቋውንና የባህሉን መስተጋብር መሰረት በማድረግ ፍቺ እንዲታወቅ ማድረጊያ፣
- አውዳዊ ጥቆማ፡- ቃላት በፅሁፍ ውስጥ ያላቸውን የእርስ በርስ ትስስር መሰረት በማድረግ ፍች እንዲታወቅ ማድረጊያ

# ምዕራፍ ሁለት

# ክላስ ድርሳናት

## 2.1 የንባብ ልምድ ምንነት

ንባብ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ መጻፍና ማንበብ) አንዱ ሲሆን መረጃ የመቀበያ ክሂል ነው። ቢሆንም የተለያዩ መረጃዎችን ከተለያዩ ጽሑፋዊ መሳርያዎች ለመቀበል በምናነብበት ወቅትም መረጃዎችን የመቀበል አቅማችን ሊለያይ ይችላል። ምክንያቱም አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት የንባብ ልምድ ወሳኝ ሚና አለው። ስለዚህ የንባብ ልምድ አንብቦ ለመረዳት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው።

ስለ ንባብ ልምድ ከማንሳታችን በፊት በቅድሚያ ልምድ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ይሆናል። ልምድ ወደዚህ አለም ስንመጣ ይዘን የመጣነውን ተፈጥሮ የምናሻሽልበት፣ የምናሳድግበትና የምናዳብርበት አብሮን የነበረ፣ አሁንም ያለ ወደፊትም አብሮን የሚኖር ከተግባርና ከተሳትፎ የሚመነጭ ክስተት ነው (አለም 2001:61)። እኚህ ምሁር አክለው እንደገለጹቱም" ልምድ ጠቃሚ ወይም ጎጂ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩልም ሆን ብለን የምንለምደው አልያም ሳናውቅ የምንለምደው ድርጊት ወይም ሁኔታ ሊኖር ይችላል። የንባብ ልምድ የምንለውም ሆን ብለን ወይም በሙሉ ንቃት የምናከናውነው ሲሆን ጠቃሚ ልምድ ተብለው ከሚፈረጁ ልምዶች ውስጥ ይካተታል። ከዚህ ሐሳብ በመነሳት የንባብ ልምድ ማለት አንድ ተማሪ መስህብነት ያለውን ጽሑፍ መርጦ ያለምንም አስገዳጅ በራሱ ውስጣዊ ግፊት ተነሳስቶ ማንበብ ሲጀምር ነው' ብለዋል።

በመሆኑም Smith (1997:29) እንደገለጹት የንባብ ልምድ የንባብ ትምህርትን አላማ በማዳበርና በማበልጸግ ላይ ያተኩራል። ይህ አይነቱ ልምድ እንዲዳብርና እንዲበለጽግ ከተፈለገ ከንባብ ጋር ያላቸውን ቀረቤታ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። ሰዎች ወደንባብ መቅረብ ይኖርባቸዋል። ሰዎች ወደ ንባብ እየቀረቡ ሲመጡ ለንባብ የሚቀመጡበት ጊዜ እየሰፋ ይመጣል። የሚያነቡት ነገር በመጠንና በገጽ ይጨምራል። ሰዎች ለንባብ የሚመድቡት ጊዜ ሲሰፋና የሚያነቡትም መጽሐፍ፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ

ወዘተ. በአይነትና በቁጥር እየጨመረ ሲመጣ ደግሞ የንባብ ልምድ አዳብረዋል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የንባብ ልምድ የሚመሰረተው የንባብን ተግባራት በተደጋጋሚ በማከናወን ነው፡፡ ይህ ማለት ተግባራቱ በተደጋገሙ ቁጥር በአእምሮ ውስጥ ሰርጾው የመግባት እድል ያገኛሉ፡፡ በአእምሮ ውስጥ ሰርጾ የገባ ነገር ደግሞ በቀላሉ የማይላቀቁት ይሆናሉ፡፡ በዚህ አይነት መንገድ ማንበብ የጀመረ አንባቢ የተዋጣለት አንባቢ እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ እንዲህ አይነቱ የተዋጣለት አንባቢ ደግሞ የሚከተሉት ሁኔታዎች ይንጸባረቁበታል (Charles, 1985፣207) ፡፡

1. ከፍተኛ የንባብ ፍላጎት

የማንበብ ልምድ ያዳበረ ተማሪ በእጆቹ በሚገቡት ለደረጃውና ለእድሜው የሚመጥኑትን መጽሐፎች፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች ወዘተ. የማንበብ ጉጉት ያድርበታል፡፡ በመሆኑም እነዚህንና የመሳሰሉት የሚነበቡ ነገሮች ገዝቶም ሆነ ተውሶ ሲያነብ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ካነበበም በኋላ ያነበበውን ቁምነገር ለጓደኞቹ ወይም ለወላጆቹ ለማጋራት ፍላጎት ይኖረዋል፡፡

2. የንባብ ፍጥነት

የማንበብ ልምድ አዳብሯል የሚባለው ተማሪ በፍጥነት ማንበብ ይችላል፡፡ ፈጣን አንባቢ የሚባለው 600 ቃላትን በደቂቃ ያነባል፡፡ ይህም በደቂቃ 200 ቃላት ወይም በታች ከሚያነቡት ዳተኛ አንባቢዎች እጅግ የላቀ ነው፡፡

3. የንባብ ስልትን መቀያየር

የማንበብ ልምድ ያዳበረ ተማሪ በሚያነብበት ወቅት እንደንባቡ አላማና እንደሚያነበው ቁምነገር የአነባበብ ስልቱን መቀያየር የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም በቀላሉ ከግርፍ ወደ አሰሳ ንባብ፣ ከሰፊ ወደ ጥልቅ ንባብ ወይም በተቃራኒው እንደአስፈላጊነቱ እያለዋወጠ ማንበብ ይችላል፡፡ በዚህ አይነት መንገድ የሚያነብ ተማሪ የማንበብ ችሎታው የላቀ ነው፡፡

4. ድምጽን ከፍ አድርጎ በእርጋታ ማንበብ

የማንበብ ልምድ ያዳበረ ተማሪ በለሆሳስ ከሚደረገው ንባብ በተጨማሪም በጮክታ ንባብም ጥሩ አቀራረብ ያሳያል። እንዲህ አይነቱ አንባቢ ድምጽን መጥናና አድማጮቹን አልፎ አልፎ እየተመለከተ በእርጋታ ማንበብ ይችላል።

5. ዘና ያለ ንባብ

የማንበብ ልምድ ያዳበረ አንባቢ በሚያነብበት ጊዜ ፊቱ ላይ የመጨነቅ ስሜት አይታይበትም። እንዲህ አይነቱ አንባቢ በለሆሳስ የንባብ ወቅትም ሆነ በጮክታ የንባብ ወቅት ስሜቱ ዘና ብሎ ይታያል። ከፍ ሲል የተዘረዘሩት ነጥቦች የማንበብ ልምድ ያዳበረ ተማሪ ወይም የተዋጣለት አንባቢ የሚያሳያቸው ባህሪያት ያመለክታሉ። ከላይ ከተገለጸው ሐሳብ እንደምንረዳው የንባብ ልምድ መሰረት ያለው ብቃት በአንባቢው ውስጥ ይቀረጻል። የንባብ ልምድ ያለው ተማሪ የምንባቡን ይዘት የሚረዳ ነው። የእውቀት አድማሱም የሰፋ ነው። ብዙ ባወቀ ቁጥርም ብዙ እንዲያነብ ያነሳሳዋል። በአጠቃላይ የንባብ ልምድ ማለት የሰዋሰው ችሎታን፣ የቃላትን ፍቺ ማወቅ፣ የአረፍተነገሮች የቃላትንና ድምጾችን በትክክል ማንበብ መቻል እንደሆነ Omaggio (1983) ገልጸዋል።

## 2.2 በንባብ ልምድ ላይ ያሉ ተጽእኖዎች

የንባብ ልምድ ከሰው ሰው የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን። ለልዩነት መፈጠር መነሻ የሚሆኑና አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅእና የሚያሳድሩ ሁኔታዎች አሉ (Carbo: 1991፣2)። እነሱም የሚኖሩበት አካባቢ፣ ውስጣዊ የስሜት ሁኔታ፣ ማህበራዊ ፍላጎት እና ስነልቡናዊ ዝንባሌ ናቸው። እነዚህን ነጥቦች እኛ ተጨባጭ የንባብ ልምድ አንፃር ስናገናዝባቸው እውነትም የሚያስኙ ናቸው። ምክንያቱም አንድ ሰው የሚኖርበት ማሕበረሰብ ንባብን እንደትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ሳይሆን ሁል ጊዜ እንደስራ የሚቆጥረው እንደሆነ ነው። የንባብ ልምድን ደካማ እንዲሆን ተፅዕኖ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ንባብን አዝናኝና አስደሳች አድርጎ አለማሰብ ነው። አለም (2001፣66-67) በንባብ ልምድ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፦

- ✓ የሰለጠነ መምህር አለመኖር፣
- ✓ በስርአተ ትምህርት ቀረጻ ላይ የሚታዩ ግድፈቶች፣

- ✓ የሕፃናት የስራ ጫና ከፍ ማለት፣
- ✓ የመጻሕፍት አቅርቦት አናሳ መሆን፣
- ✓ የቴሌቭዥን የቪድዮ እና የኮምፒዩተር ጨዋታዎች መስፋፋት፣
- ✓ የመጻሕፍት የስርጭት አውታሮች ቁጥር አናሳ መሆን፣
- ✓ የቤተ መጻሕፍት አለመስፋፋት ፣
- ✓ በህብረተሰቡ ዘንድ ለንባብ ያለው አመለካከት የተዛባ መሆን፣
- ✓ የመገናኛ ብዙሃን ለመጻሕፍትና ለንባብ ትኩረት አለመስጠት ፣
- ✓ የሰዎች የንባብ ፍላጎት ማጣት የሚሉት ይገኙበታል።

በአጠቃላይ የንባብ ፍላጎት ለንባብ ችሎታ መዳበር አንዱና ትልቁ መሰረት ነው። ስለዚህ የንባብ ፍላጎት አለመኖር፣ በቂ የመጻሕፍት አቅርቦት አለመኖርና የቤተ መጻሕፍት አለመስፋፋት የንባብ ልምድ እንዳይዳብር ከሚያደርጉ ነጥቦች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

## 2.3. የንባብ ልምድ ማጐልበቻ መንገዶች

የንባብ ልምድ የሚጐለብተው የተለያዩ ፅሁፎችን በተለያዩ አጋጣሚዎች በማንበብ ነው። የተሻለ የንባብ ልምድን ለማጎልበት ያስችላሉ ተብለው በተለያዩ ምሁራን ከተጠቀሱት መንገዶች ጥቂቶቹ በትምህርት ቤት ውስጥ የተለያዩ ፅሁፎችን ማንበብ፣ ከትምህርት ቤት ውጭ ማንበብ፣ የጥቆማ ዘዴዎችን በንባብ ጊዜም አገባቡ መጠቀም፣ እንዲሁም ወደተሻለ አንባቢነት የሚያስጠጉ ባህሪያትን አውቆ በተግባር ላይ ማዋል የሚሉት ናቸው (May 1990:39; Millan 1991:32)።

### 2.3.1. በትምህርት ቤት ውስጥ የንባብ ልምድን ማጎልበት

የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ለማጎልበት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ በክፍልና ከክፍል ውጭ የሚያደርጉት የማንበብ ልምምድ እንደሆነ ይታወቃል። ይህም ተማሪዎቹ በመምህራን እገዛ የሚያደርጉትን የማንበብ ልምምድ፣ እንዲሁም እርስ በርስ የሚያደርጉትንና በግላቸው የሚያከናውኑትን ልምምድ ሁሉ ያጠቃልላል (Silberstein1994:78)።

Carrel and Define(1995፣45) እንደሚገልጹት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የንባብ ልምዳቸውን የሚያጎለብቱበት መንገድ ማንበብ እንዴት መማርና ማከናወን እንዳለባቸው በግልጽ ሲነገራቸው ነው፡፡በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ማንበብን በሚያለማምዱበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ስልቶችም ስለሚያነቡት ጽሑፍ ተማሪዎቹ ያላቸውን እውቀት በቅድሚያ መጠየቅ፣ የጽሑፉን አጠቃላይ መልዕክት መጠቆም፣ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማሳወቅ፣ጽሑፉን በምን ዓይነት መንገድ ማንበብ እንዳለባቸው ማስረዳት የሚሉት ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪ ይህንን ሐሳብ በማስመልከት (Silberstein 1994፣78) እንደሚያብራሩት መምህራን የተማሪዎቻቸውን የንባብ ልምድ ለማጎልበት ተማሪዎችን በግልና በቡድን በማደራጀት የተለያዩ ጽሑፎችን በማደል የንባብ ዓላማን ሊያሳካ የሚችል የአነባበብ ስልት መርጠው እንዲጠቀሙ ማለማመድ አለባቸው፡፡ ይኸውም እያንዳንዱን ጽሑፍ በምን ዓይነት ስልት እንደሚያነቡ መንገርና የተመ ረጠውን ስልት በአግባቡ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ማረጋገጥ ተገቢነት አለው፡፡

ይህንን ሐሳብ አስመልክተው Key (1979:93) እንደገለፁት ተማሪዎቹ ታዘው ከሚያነቡ ዋቸው ፅሁፎች የተወሰኑትን በክፍል ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም እንግዳ አይሆንባቸውም፤ ቀድመው ባነበቡት በመታገዝ እንዲመልሱ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለማንበብ ፍላጎታቸውን ስለሚያነሳሳው ለወደፊቱ በርካታ ፅሁፎችን እያነበቡ የንባብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ከዚህም ሌላ መምህራን በክፍል ውስጥ ንባብን በሚያለማምዱበት ወቅትም ሁሉም ተማሪዎች በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ የንባብ ልምዳቸውን ለማጎልበት ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው፡፡

በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ መፃህፍትን በማስነበብ ብቻ የተማሪዎችን የንባብ ልምድ በሚፈለገው ደረጃ ለማጎልበት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በትምህርት ቤት ውስጥ ከክፍል ውጭ የሚያነቡበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም መምህራን ተማሪዎቹ የተለያዩ ፅሁፎችን የሚያገኙበትን መንገድና የፅሁፎችን አይነት ለይቶ በመጠቆም በኩል የበኩላቸውን ሚና መጫወት አለባቸው፡፡ ይህንንም ለማድረግ መምህራን በቅድሚያ በትምህርት ቤቱ ቤተ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙትን

ለንባብ የሚያግዙ ፅሁፎች መለየት አለባቸው፡፡ እንዲሁም በትምህርት ቤቱ የማይገኙ አጋዥ የንባብ መፃህፍት የሚገኙበትንና የሚገዙበትን ሁኔታ መጠቆም አስፈላጊ ነው (Arcy 1973፣111)፡፡ ይህ ሲደረግ ግን መምህራን ለተማሪዎቹ በመጀመሪያ መሰረታዊ የንባብ ክሂልን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ በቅድሚያ መሰረታዊ የማንበብ ክሂልን ካላዳበሩ የሚቀርቡላቸውን መጻሕፍት በግላቸው በአግባቡ አንብበው ልምዳቸውን ማጎልበት ስለማይችሉ ነው፡፡

Key (1979:89) በArcy (1973:111) ሃሳብ የሚስማሙ ሲሆን መምህራን በርካታ መፃህፍት ለተማሪዎች ካቀረቡላቸው በኋላ የፈለጉትን መርጠው እንዲያነቡ እድሉን ለተማሪዎች መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በራሳቸው ምርጫ መፃህፍትን እንዲያነቡ ማድረግ ለወደፊቱ በርካታ መፃህፍትን በግላቸው እየመረጡ በማንበብ ልምዳቸውን ለማጎልበት ያበረታታቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ለማጎልበት መምህራን በክፍል ውስጥ የተማሪዎቹን የንባብ ፍላጎት የሚያነሳሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም Farratnt, (1977)ን በመጥቀስ Conley (1992:28) እንዳብራሩት ለማንበብ አዎንታዊ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የተለያዩ ፅሁፎችን እያነበቡ ልምዳቸውን በጥሩ ሁኔታ ሊያጎለብቱ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪ Gray, እና Staiger (1969፣52) የማንበብ ፍላጎት መኖር ከማንበብ ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞችን ሁሉ ለማግኘት እጅግ አስፈላጊና መሰረታዊ ነገር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

### 2.3.2. ከትምህርት ቤት ውጭ የንባብ ልምድን ማጎልበት

የተማሪዎች የንባብ ልምድ የሚጎለብትበት አንዱ መንገድ በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚያደርጉት የንባብ ልምምድ ቢሆንም በትርፍ ጊዜያቸው ከትምህርት ቤት ውጭ በሚያደርጉት ልምምድም ልምዳቸውን ለማዳበር ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ በበርካታ ምሁራን ተገልጿል፡፡ ከነዚህ መካከል Greenall እና Swant (1996፣69) ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ በግላቸውም ሆነ በቤተሰቦቻቸው እገዛ ሰፊ የማንበብ ልምምድ ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው ይገልጻሉ፡፡ ይህ ማለት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ የተለያዩ ፅሁፎችን እያነበቡ የንባብ ልምዳቸውን እንዲያጎለብቱ ወላጆች እገዛ ማድረግና ማበረታታት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ነው፡፡

May (1990) በበኩላቸው "ጥሩ የንባብ ልምድ እንዲኖራቸው የሚፈለጉትን ተማሪዎች ማንበብን የሚወዱና የሚችሉ ሞዴል አንባብያን በአካባቢያቸው ሊኖራቸው ይገባል" ይላሉ። ይህ አባባል የሚያመለክተው ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከትምህርት ቤት ውጭም በቅርብ የሚያገኙትና የሚያዩት ጥሩ አንባቢ መኖር ወይም አለመኖር የእነሱን ፍላጎት አነሳስቶ እንዲያነቡ ወይም ልምዳቸውን እንዲያጎለብቱ ወይም እንዳያጎለብቱ በማድረግ ረገድ የራሱ ተፅዕኖ እንዳለው ነው። Conleyም (1992፣62) እንዳብራሩት ከተማሪዎች ቤተሰቦች ውስጥ ጥሩ አንባብያን ኖረው ለልጆቹ በተለያየ ጊዜያት ልዩ ልዩ ፅሁፎች የሚያነቡላቸውና እነሱም እንዲያነቡ የሚገፋፋቸውና የሚያበረታታቸው ከሆነ ልጆቹ ጥሩ የንባብ ልምድን አጎልብተው ያድጋሉ።

ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ ማበረታታት የራሱ ከፍተኛ ጥቅም አለው። ከትምህርት ቤት ውጭ በሚያነቡበት ጊዜ የራሳቸው ነፃነት እንዲሰማቸው ስለሚያደርግ በፈለጉት ፍጥነትና ጥልቀት ፅሁፉን አንብበው የመረዳት ችሎታን ያዳብራሉ፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ በመምህራን ጥብቅ ቁጥጥር ከሚደረገው የማንበብ ልምምድ ይልቅ ተማሪዎቹ መሰረታዊ የማንበብ ክሂሎችን ካዳበሩ በኋላ ከትምህርት ቤት ውጭ በግላቸው የሚያነቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ጥሩ የንባብ ልምድ እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል (Chubby, 1991)።

በተጨማሪ Chubby (1991፣65) አክለው እንደገለጹት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ ማድረግ በክፍል ውስጥ ከሚቀርቡላቸው ውስን ፅሁፎች ይልቅ በይዞታቸው፣ በቅርፃቸው የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲያገኙና እንዲያነቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ፅሁፎች በሚያነቡበት ጊዜ የተለያየ ቅርፅና ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች የማንበብ ልምድን ያዳብራሉ፡፡ እንዲሁም ለወደፊት በራሳቸው ምርጫና ዝንባሌ መሰረት የተለያዩ ፅሁፎችን እያነበቡ ልምዳቸውን ለማጎልበት ያስችላቸዋል።

### 2.3.3. በንባብ ጊዜ ጠቋሚ ዘዴዎችን በአግባቡ መጠቀም

የአንድን ፅሁፍ መልእክት ለመረዳት የሚያግዙ ጠቋሚ ዘዴዎች ተብለው የሚገለጹት ስነ አገባባዊ ጥቆማ፣ ስነ መዋቅራዊ ጥቆማ፣ ስነ-ድምፃዊ ጥቆማ፣ ባህላዊ ጥቆማና ዳራዊ ጥቆማ ናቸው (May 1990:42 እና Millan, 1991፡48) ፡፡ ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ በሚያነቡበት ወቅት ቢያንስ የተወሰነውን የፅሁፉን ይዘት መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም የፅሁፉን ይዘት ለመረዳት ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ይዘቱን በአግባቡ እንዳይረዱ የሚያደርጉ መሰናክሎች በፅሁፉ ውስጥ ያጋጥሟቸዋል እነዚህን መሰናክሎች አስወግደው የፅሁፉን መልእክት ለመረዳት በንባብ ጊዜ የጠቋሚ ዘዴዎች አጠቃቀም ከንባብ ልምዳቸው ጋር አብረው አዳብረው መገኘት ይኖርባቸዋል (Bastidas 1984፡74)፡፡ እኚሁ ምሁር በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ ጠቋሚ ዘዴዎች የፅሁፉን መልእክት ለመረዳት አንብበው ማወቅ ያለባቸው ቁልፍ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ጠቋሚ ዘዴዎች አጠቃቀም እውቀትንና ልምድን አጎልብቶ የተገኘ አንባቢም ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ ሳያስፈልገው የሚያነበውን ፅሁፍ መልእክት በአግባቡ ይረዳሉ በማለት ገልጸዋል ፡፡

በመሆኑም ጥሩ የንባብ ልምድ ያጎለበቱ አንባብያን የሚባሉት ልዩ ልዩ ፀሃፊዎች በፅሁፋቸው ውስጥ ማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልእክት ለአንባቢያን ግልፅ ለማድረግ አስበው የሚጠቀሙባቸውን የጥቆማ ዘዴዎች አውቀው መገልገል የሚችሉ ናቸው፡፡

## 2.4 የአንባቢያን ዓይነቶች

### 2.4.1 ብቁ የሆኑ አንባቢያን

ብቁ የሚባሉት አንባብያን አንድን ፅሑፍ ሲያነቡ ፅሁፉን የመገምገምና በፅሑፍ ዙሪያ የራሳቸውን ጥያቄ እያነሱ ምላሽ የመስጠት ልምድ አላቸው፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት የፅሑፉን መሰረታዊ ሀሳብ ይበልጥ ለመረዳት፣ እውነትነት እንዳለው ለማረጋገጥ እንደሚያግዛቸው ስለሚረዱ ነው፡፡ ይህንንም Millan(1991፣35) ሲያስረዱ "ብቁ አንባብያን ሃሳባቸውን በራሳቸው አባባል ለመግለፅ ይሞክራሉ፣ በፅሁፍ ውስን ወጭ የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ" ይላሉ፡፡ ይህም ማለት አንባብያኑ ከጽሑፉ አውዳዊ ፍች ውስጥ ያለው ትርጉምን ያስተውላሉ፡፡

ብቁ አንባቢያን አውዳዊ ጥቆማዎችንና የግል የሕይወት ልምዳቸውንና እውቀታቸውን መሰረት በማድረግ አንድን ፅሁፍ ሙሉ በሙሉ ከማንበባቸው በፊት ርእሶቹን በመቃኘት

ስለአጠቃላይ መልዕክቱ የመተንበይ ልምድ አላቸው ትንበያቸውም ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ስለሚገፋፋ ፅሁፉን ፈጥነው ማንበብ ይያያዙታል (Silberstein 1994)፡፡

በተጨማሪ Niles(1972) እንደሚያብራሩት ብቁ አንባብያን ከአሁን በፊት የሚያውቁትን ቃል በሚያገኙበት ጊዜ ከቃሉ አውድ በመነሳት ወይም የቋንቋውን የሥነ-ድምፅ አወቃቀር በመገንዘብ፣ ከዓረፍተነገሩ አወቃቀርና አውድ በመነሳት አጥርቶ የማንበብ ልምዳቸውን የዳበረ ነው፡፡ ስለሆነም በፅሁፍ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ሃሳብ መገንዘብና ዋናውን ሐሳብ ለመዘርዘር የተገለፁትን ዝርዝር ዓረፍተነገሮች በደንብ መረዳት የሚችሉ ናቸው፡፡ ለዚህም የዝርዝር ሐሳቦችን ቅንጅት፣ አንድነትና ልዩነት በደንብ መረዳት የሚችሉ ሲሆኑ በተጨማሪ አንድ ሐሳብ በተለያዩ መልክ ሲገለፅና ሲቀነባበር መቻሉን የሚገነዘቡ ናቸው፡፡
በአጠቃላይ ብቁ አንባቢያን ቀደም ሲል ካነበቡት ወይም ካለፉ ልምድ፣ ትምህርትና የሕይወት ገጠመኝ በመነሳት ከቀረበው ፅሑፍ ባሻገር ጉዳዮን በጥልቀት መመልከት፣ትንታኔ መስጠት የሚችሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንባቢው ከተፃፈው ጉዳይ ተነስቶ የእራሱን ፍቺ፣ ሐሳብና አስተያየት የመስጠት ችሎታውን ማዳበር የሚችል መሆኑን Niles (1972) ገልፀዋል፡፡

### 2.4.2 ብቁ ያልሆኑ አንባብያን

ብቁ ያልሆኑ አንባብያን በግል ንባብ ወቅት በፀጥታ ከማንበብ ይልቅ በጮክታ ሲያነቡ ይታያሉ፡፡ እነዚህ አንባብያን በጮክታ በሚያነቡበት ጊዜ ፍጥነታቸውን ከመግታቱም በተጨማሪ መልእክቱን ለመረዳት እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡ በመሆኑም ፅሁፉን አንብበው ሲጨረስ- ጥያቄ በሚጠየቁበት ጊዜ እንደገና ወደኋላ በመመለስ ለማንበብ ጥረት ሲያደርጉ ያስተውላል፡፡ በዚህም ምክንያት በአጭር ጊዜ የሚሰሩ የምንባብ ፈተናዎችን ሲፈተኑ አነስተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ (Badraw 1992፣102)፡፡

## 2.5. ብቁ የሆኑና ያልሆኑ አንባብያን አበይት ባህሪያት

ሁሉም አንባብያን የማንበብ ክንዋኔን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያሳዩአቸው ግላዊ ባህሪያት አሏቸው፡፡ በመሆኑም የተለያዩ አንባቢያንን የሚያሳዩአቸውን ልዩ ልዩ ባህሪያት መሰረት በማድረግ አንባብያንን በተለያዩ ደረጃዎች መመደብ እንደሚቻል ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

Conley (1992፥69) ጠቅለል ያለ ባህሪያትን በማየት አንባብያን ብቁና ብቁ ያልሆኑ በሚሉ ሁለት ክፍሎች በመመደብ ይገልጻሉ፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር ብቁ የሆኑ ወይም ያልሆኑ ተብለው በአንድ ወይም በሌላ ክፍል የሚመደቡት አንባቢያን በመካከላቸው በጋራ ከሚያሳዩአቸው ጉልህ ባህሪያት ውጭ የተወሰነ ልዩነት አይታይም ማለት አይደለም፡፡ ከዚህ በታች ብቁ የሆኑና ብቁ ያልሆኑ አንባብያን አበይት ባህሪያት በተናጠል በዝርዝር ቀርበዋል፤

### 2.5.1. ብቁ የሆኑ የአንባብያን ባህሪያት

ብቁ አንባብያን የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን ከማወቃቸው የተነሳ አንድን ፅሁፍ በአንድ ስልት እየተጠቀሙ ሲያነቡ ሐሳቡን ለመረዳት ሲያስቸግራቸው ሌሎች የተለያዩ ስልቶችን አማርጠው የመጠቀም ባህሪ አላቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ብቁ አንባብያን የዳበረ ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ የሚያነቡት ፅሁፍ አንዳንድ ጉድለቶችና ስህተቶች ካሉት አሚልተውና አርመው የማንበብ ባህሪ አላቸው (May 1990፥12)፡፡

Conley (1992፡69) እንዳብራሩት የብቁ አንባብያን ባህሪያት የሚባሉት እንደሚከተለው ያስቀምጧቸዋል፡፡

- የአንድን ፅሁፍ ይዘት ለመረዳት ችግር ሲገጥማቸው የሚጠቀሙባቸው አማራጭ ስልቶች ያልገባቸውን ቃል አልፈው ሌሎቹን በማንበብ አጠቃላይ መልእክትን መረዳት፤
- ቀድሞ የሚያጋጥም ፅንሰ ሐሳብና የመረዳት ችግር ቀጥሎ በመጣው ሐሳብ በመታገዝ መረዳት፣
- ሚዛናዊ በሆነ ግምት ቃላትን መተርጎም፣

- በቅርብ ያለፉትን ዐ/ነገር ተመልሶ በድጋሚ ማንበብና ተዛማጅ ፅሁፎች

  በማንበብ ሀሳብን መረዳት፣

- ፅሁፉን የተሟላ የሚያደርጉባቸው ስልቶች የተወሰኑ አገላለፆችን በራሳቸው

  አባባል በመተካት ማንበብ፣

- የፅሁፉን አደረጃጀት አስተካክሎ በማንበብ፣

- የሐረጋትና የቃላት ጉድለትን አሟልቶ በማንበብ እና የስርዓተ ነጥቦችን ስህተት

  አስተካክሎ ማንበብ ናቸው ።

በአጠቃላይ ብቁ አንባብያን ሲያነቡ የራሳቸውን ስሜት ብቻ ሳይሆን የፀሐፊውን ስሜት፣ ፍላጎትና እምነት ጭምር የመመርመርና የመረዳት ባህሪ አላቸው (May 1990)። በተጨማሪም በአንድ ጊዜ እይታ በርካታ ቃላትን እየቃኙ ጽሑፉን በተገቢው ፍጥነት አንብበው የመጨረስ ባህሪ አላቸው። በረጃጅም ዓረፍተነገሮች የተሟላ ጽሑፍን ሳይቀር በአንድ ትንፋሽ ሊያነቡት ወደሚችሉት አነስተኛ ክፍሎች እየቆራረጠ በማንበብ በአጭር ጊዜም ምንባቡን አዳርሰው ሐሳቡን ለመገንዘብ ይችላሉ (Badraw 1992)።

2.5.2. ብቁ ያልሆኑ የአንባብያን ባህሪያት

ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ካላቸው አነስተኛ የንባብ ልምድ የተነሳ ትክክለኛ የአነባበብ ስልትን ተከትለው ስለማያነቡ ጊዜያቸውን በከንቱ ከማጥፋታቸውም ሌላ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ ነው። እነዚህ አንባብያን አንድን ፅሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ በጋራ የሚንጸባረቁባቸው በርካታ ባህሪያት አሏቸው። ከነዚህም የጋራ ባህሪያት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው (May, 1990፣14)፤

ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ማንበብን የሚገነዘቡት በፅሑፍ ውስጥ የሰፈሩትን ቃላት እንደማነብነብ ወይም እንደመጥራት ነው። ስለሆነም የተፃፉትን ቃላት ማነብነባቸውን እንጂ የፅሁፉን ይዘት መረዳት አለመረዳታቸውን እምብዛም ትኩረት አይሰጡትም።

ከዚህም ሌላ ብቁ ያልሆኑ አንባብያን አንድን ፅሁፍ ሲያነቡ ቃላትንና ሀረጋትን እያያዙ ከማንበብ ይልቅ በእያንዳንዱ እይታቸው አንድ ነጠላ ቃልን ወይም የቃሉን ክፍል በመቃኘት ብቻ የማንበብ ባህሪ አላቸው። በዚህም ምክንያት በአንድ ጽሑፍ

ውስጥ የተካተቱ ሀረጋት፣ዐረፍተ ነገሮችና አንቀፆች እርስ በርስ ተቀናጅተው የሚያስተላልፉትን መልእክት ለመረዳት ከመቸገራቸው በላይ ፍጥነታቸው ዘገምተኛ ነው፡፡ እንዲሁም ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ የተወሰነ መረጃን ብቻ ነጥሎ ለማውጣት የሚያስችል የአነባበብ ስልትን ለማዳበር አያስችላቸውም (Farrant 1977)፡፡

በአጠቃላይ Conley (1992፡72) ሲገልጹ ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ስለ ንባብ ምንነት ካላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ የተነሳ አንዱን ፅሁፍ ሲያነቡ ሀሳቡ የማይገባቸው ከሆነ ፅሁፍን ቃል በቃል ለመሸምደድ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም ፅሁፉን ካነበቡ በኋላ ስለ ፅሁፉ የፅንስ ሀሳብ ጥያቄ ሲጠየቁ አገናዝበው ከመመለስ ይልቅ የሸመደዱት እንዳለ ቃል በቃል የመመለስ ባህሪ ይታይባቸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የብቁ አንባብያንና ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ባህሪያትና ምንነት መሠረት በማድረግ የተማሪዎች የንባብ ልምድ ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንደመስፈርትነት ሊያገለግለን ይችላል ፡፡

## 2.6. አንብቦ መረዳት

### 2.6.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ማለት ያነበቡትን ምንባብ እንዲሁ መቀበል ወይም አለመቀበል ሳይሆን ከዚህ በተለየ መልኩ ስለ አነበቡት ምንባብ እራስን መጠየቅን፣ የምንባቡን አጠቃላይና ዝርዝር ሀሳብ መመርመርን፣ ማመዛዘንንና ቀደም ሲል ካለ እውቀት ጋር ማመሳከርን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን ተስፋዬ (1986፡9) ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ አንድን ፅሑፍ አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነው፡፡

Grellet, (1981:3) በበኩላቸው "አንብቦ መረዳት ማለት ከፅሁፍ ውስጥ የተፈለገውን ሀሳብ በተቻለ መጠን በብቃት ማውጣት ማለት ነው" ይላሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው ተማሪው ምንባቡን የሚያነብበትን አላማ ተረድቶ የተጠየቀውን ሀሳብ ካወጣ አንብቦ መረዳቱን ያመለክታል ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም ተማሪው የምንባቡን ርዕስ መሰረት በማድረግ ወደ ፊት በምንባቡ ውስጥ ምን ሊመጣ እንደሚችል ይተነብያል ወይም ራሱን ይጠይቃል፡፡ለጠየቀውም

ጥያቄ መልስ ማግኘት ሲችል አንብቦ የተረዳ መሆኑን Smith (1973) ይገልፃሉ፡፡ አክለውም "መተንበይ ጥያቄ መጠየቅ ሲሆን፣ አንብቦ መረዳት ደግሞ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ነው" ይላሉ፡፡ ይህም ማለት አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ መጠየቅን፣ ማመዛዘንን፣ መመራመርን፣ ማመሳከርን ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች ያነበቡት ነገር በደፈናው ከመቀበል ወይም ካለመቀበል አልፈው የመገንዘብ ችሎታ የሚያጠቃልላቸውን ተግባራት ይፈፅማሉ፡፡

ይህ ለአንብቦ መረዳት መሰረት የሆነው ትንበያ የሚገኘው ስለ ነባራዊው አለም ያለንን ዕውቀት በመጠቀም መሆኑን Smith (1973) ገልፀዋል፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተማሪው አንብቦ ከመረዳቱ በፊት እንደሚተነብይና ትንበያውም መሰረት የሚያደርገው ርእሱን /የሚያነበውን ነገር/ በተመለከተ ተማሪው ከዚህ በፊት ባለው እውቀት ላይ መሆኑን ነው፡፡

### 2.6.2. የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች

በፍጥነትና ደረጃውን በጠበቀ ስልት ማንበብ የሚኖርብን ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሲነሳ መልሱ አንብቦ ለመረዳት ነው፤ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንብቦ መረዳት በውስጡ ብዙ ንዑሳን ክሂሎችን ያካተተ ነው (ማረው 1997)፡፡ ከነዚህን ንዑሳን ክሂሎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

#### 2.6.2.1. የቃላትና ሀረጎችን ፍች መረዳት

አንባቢው በጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት አውዳዊ ፍቺ ሊረዳ ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጂ የጽሑፍን መልዕክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ማወቅ የግድ አስፈላጊ ስላልሆነ አንባቢው በጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት ፍቺዎች አንድ በአንድ መመርመር አይጠበቅበትም (Grellet 1981፡5)፡

#### 2.6.2.2. የጽሑፍን ግልጽ መልዕክት (Explicitly Stated information) መገንዘብ

አንባቢው በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት እና ይህንን መልዕክት ለማጉላትም ሆነ ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ሐሳቦችን መረዳት አለበት (Greenwood, 1981፡89)፡፡

2.6.2.3 የጽሑፉን ውስጣዊ (Implicitly stated Information ) መልዕክት መገንዘብ

በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ የቀረበውን መልዕክት መገንዘብ አንብቦ የመረዳት ዋነኛ አካል ቢሆንም አንባቢው በዚሁ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት መነሻ በማድረግ፣ በማገናዘብና በመመርመር የሚደረስበትን ውስጣዊ መልዕክትም መረጃነት ይጠበቅበታል (Greenwood, 1981፣90)።

2.6.2.4 የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ ሃሳብ ፍሰተ መገንዘብ

አንባቢው በጽሑፍ ውስጥ ያሉትን ረፍተነገሮች ተናጠላዊ መልዕክት መረዳት ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ ባሻገርም የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ የሃሳብ አገላለጽ፣ አንዱ ዓረፍተነር ከፍተኛውና ከተከታዮቹ ዓረፍተነገሮች ጋር ያለውን የሐሳብ ግንኙነት የጽሑፍ የተለያዩ አንቀፆች ያላቸውን የርስ በርስ ግንኙነት ሊረዳ ይገባዋል (Heaton:1975:103)።

2.6.2.5 የአያያዦችን ሰዋስዋዊ አገባብና ትርጉም መረዳት

Grellet (1981፣6) ሲገልጹ አንድ አንባቢ በሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ፣ አገልግሎትና ትርጉም መገንዘብ ይጠበቅበታል።እነዚህን መገንዘቡን የጽሑፉን መልእክት ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክቱለታል።

አያያዥ ቃላት ቃልን ከቃል፣ ሐረግን ከሐረግ አረፍተነገርን ከአረፍተነገር፣ የሚያጣምር ነው። አያያዥ ቃላት በተለይም የመስተፃምር ዋና ባህሪው አቻ የሆኑ ነገሮችን እያጣመሩ ሰፋ ያለ ሐረግ መመስረት ነው። ተጣማሪዎቹ ቃል እና ቃል ወይም ሐረግና ሐረግ መሆን አለባቸው። መስተፃምራዊ ሐረግ አንድን ቃል በሌላው ስር የሚያሳድር ወይም የሚያዋቅር ሳይሆን ሁለቱን ቃላት በአቻነት ወይም በእኩልነት የሚያገናኝ ሐረግ ነው። ተጣማሪዎች በመጠናቸው አቻ፣ በቃል ክፍላቸውም አንድ አይነት መሆን አለባቸው። ተጣማሪዎች የነገሮችን ተመጣጣኝ ብቻ ሳይሆን በሚገልጹት ሐሳብም የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው ይሁን እንጅ የማይጣጣሙ ወይም የሚጻረሩ ሐሳቦችን የሚገልጹ ሌሎች መስተፃምሮችም አሉ ለምሳሌ፡- ነገርግን፣ ይሁንእንጂ፣ ቢሆንም፣ ወዘተ. (ባየ 2002፡193)።

አያያዥች ለአንባቢያን ፍንጭ በመስጠት ግልፅ ያልሆነውን ሃሳብ ለመረዳትና የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመገመት ያስችላሉ፡፡ "ግጥምጥምነት በአንቀፅ ውስጥ የሚገኙትን አረፍተ ነገሮች መያያዝ ይመለከታል፡፡ይህን ግጥምጥምነት ለማስጠበቅም ከያኒው መስተፃምርንና የመሸጋገሪያ ሀረጋትን በሚገባ መገልገል አለበት፡፡ ለአያያዥነት ያገለግሉታልና" ተስፋዬ (1980፣ 48-49)፡፡

## 2.7. የንባብ ስልቶች

### 2.7.1. የፍጥነት ንባብ /Scanning/

የፍጥነት ንባብ ከምንባቡ ውስጥ የምንፈልገውን መረጃ ለማግኘት አይናችንን በፍጥነት በማንቀሳቀስ የምናነብበት፣ ስልት መሆኑን (Grellet 1981) ይገልፃሉ፡፡ ይህም ለፍጥነት ንባብ በፍጥነት ማንበብ ተገቢ መሆኑንና ከምንባቡ ውስጥ የተወሰነ መረጃን ማግኘት ሳይሆን የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ፣ የምንባቡን አደረጃጀትና ፀሃፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሀሳብ ለመገንዘብ እንደሚያገለግልና ለዝርዝር ሀሳቦች ትኩረት እንደማይሰጥ ያመለክታሉ፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ ከቃል ይልቅ በአረፍተ ነገር ደረጃ የተገለፀን እውነታ እንዲመለከቱ ወይም ምንባቡ ስለምን እንደሆነ እንዲገልፁ ሲጠየቁ ወይም ምንባቡን በፍጥነት አንብበው የሚመልሷቸው የተወሰኑ ጥያቄዎች ሲሰጧቸው የፍጥነት ንባብ ስልትን እንዲጠቀሙ Nutal (1982፡40) ይገልፃሉ፡፡

### 2.7.2. የአሰሳ ንባብ /Skimming/

የአሰሳ ንባብ አይናችንን በፍጥነት በማንቀሳቀስ የምንፈልገውን ስም፣ ቀን፣ አመተ ምህረት፣ አንድ ቃል ስንት ጊዜ እንደተደጋገመ፣ ከማውጫ ገፅ የተወሰነ መረጃን ለማውጣት ይጠቅማል (Grellet 1981 እና Nuatll 1982)፡፡ በአሰሳ ንባብ የሚፈለገውም አጠቃላይ ወይም ዝርዝር ሀሳብ ሳይሆን የተወሰነ መረጃን ከምንባቡ ፈልጎ ለማግኘት የቃላት ድግግሞሽን ለማየት፣ ስሞችን፣ ቀኖችን፣ ዓመተ ምህረትንና የተለያዩ መረጃዎችን በፍጥነት አይንን በምንባቡ ላይ በማንቀሳቀስ ለይቶ ለማውጣት የሚያገለግል ስልት ነው፡፡

### 2.7.3. ጥልቅ ንባብ /Intensive Reading/

ጥልቅ ንባብ በመምህሩ የቅርብ ክትትል /አጋዥነት/ ወይም በምንባቡ መሪነት ተማሪዎቹ ለምንባቡ ይዘት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚያነቡበት ስልት ነው፡፡ ዋና ኣላማውም ተማሪዎቹ የምንባቡን ሀሳብ በዝርዝርና በጥልቀት እንዲረዱና የምንባቡ መልዕክትም እንዲመረምሩ ማድረግ መሆኑን Nuatall (1982) ገልፀዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው አንድን ምንባብ በትኩረት በማንበብ ዝርዝር መልዕክቱን መገንዘብ ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱን ቃል፣ ሀረግ፣ አረፍተ ነገር ከፍ ሲልም የአንቀፅ አደረጃጀትና በምንባቡ ሊተላለፍ የፈለገውን ጥልቅ መልዕክት የሚመረምርበት የንባብ ስልት ነው፡፡

በተጨማሪም Grellet (1981:4) እና Nuatall (1982:23) ስለጥልቅ ንባብ ሲገልፁ ከሰፋፊ ምንባቦች ይልቅ አጫጭር ምንባቦችን መጠቀም በጥልቅ በማንበብ የተወሰነ ሀሳብን በትክክል ለማግኘትና ለመቆጣጠር አመቺ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ይህም በጥልቀት በሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ ውስጥ ያሉ እያንዳንዳቸውን ነገሮች ማጤን ስለሚገባ መጠናቸው ሰፊ ከሆኑ ምንባቦች ይልቅ በአጭር ምንባቦች መጠቀም የተሻለ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

## 2.8 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ አሰጣጥ

የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመመዘን በዋነኛ መሳሪያነት የሚያገለግለው አንብቦ የመረዳት ፈተና እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ተፈታኞቹ በፈተናው ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ይቻላል (Nuttal, 1982፣37 Kavale, 1979፣27 Fry, 1963፣iii)፡፡

Nuttal (1982፡37) እንደሚገልጹት የአንድን ተማሪ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተሰጠው አንብቦ የመረዳት ፈተና ባገኘው ውጤት ማወቅ ይቻላል፡፡ ተፈታኙ በፈተናው ያገኘው ውጤት 70% ከሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ነው ከሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ Narayunaswamy (1975:144) እንደሚያስገነዝቡትም በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ በተለመደው ፍጥነት በማንበብ በሚሰራው አንብቦ የመረዳት ፈተና 70% (ፐርሰንት) ሊያገኝ ይገባዋል ፡፡ የፈተናው ውጤት ከ70% በላይ ከሆነም ጥሩ ችሎታ አለው ሊባል ይችላል፡፡ የተፈታኙ ውጤት 50% ወይም ከዚያ

በታች ከሆነ ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ተማሪው በተሰጠው ፈተና ያገኘው ውጤት ከ70-80% ከሆነ በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው። ከ50-60% ወይም ከ5-6 ከአስር ውጤት ካገኘ ችሎታው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል (Fry, 1963፣ iii)።

Kavale (1979፣27) እንደሚያስገነዝቡትም በአንብቦ የመረዳት ፈተናው 90 ወይም ከዚያ በላይ ከ100 ያገኘ ተማሪ ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው። ከ75-90 ከመቶ ያገኘ ተማሪ ችሎታም በቂ ከሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል። ውጤቱ ከ70 ፐርሰንት በታች ከሆነ ግን ችሎታው ዝቅተኛ ነው ።

አንድ በአፍ መፍቻ ቋንቋው በቂ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ አንብቦ የመረዳት ፈተና ማግኘት ያለበትን ውጤት በተመለከተ Nuttal (1982:37) and Narayunaswamy(1975:144) በተመሳሳይ ውጤት ይስማማሉ ማለትም ተፈታኙ በፈተናው ያገኘው ውጤት 70 ፐርሰንት ከሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታው በቂ ነው በሚለው ሃሳብ ይስማማሉ Fry(1963:iii) and Kavale (1979:27) የሚስማሙበት በተመሳሳይ ውጤት ቢሆንም ከላይኞቹ ጋር የጎላ ልዩነት የለውም። ማለት Fry የአንብቦ መረዳት ችሎታው በጣም ዝቅተኛ የሚለው ነጥብ ከ 50 በታች ሲሆን Kavale ግን ከ 70 በታች ይለዋል በዚሁ ነጥብ ሁለቱም ይለያያሉ።

ከዚህ በላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታደረጃ አሰጣጥ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በሰነዘሩዋቸው ሐሳቦች መሰረት ተማሪዎች በሚሰጣቸው የአንብቦ መረዳት ፈተና ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት የሚገኙበት ደረጃ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

## ሠንጠረዥ 1፡- አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ

| ውጤት | ደረጃ |
|---|---|
| ከ100-90 | በጣም ከፍተኛ |
| ከ91-75 | ከፍተኛ |
| ከ75-61 | መካከለኛ (በቂ) |
| ከ60 በታች | ዝቅተኛ |

በአጠቃላይ የንባብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚጎለብትበት የተለያዩ ፅሁፎችን በተለያዩ አጋጣሚዎችና የጊዜያት በማንበብ ነው። ጥሩ የንባብ ልምድን

ለማጎልበት ያስችላል ተብለው በተለያዩ ምሁራን ከተጠቀሱት መንገዶች ጥቂቶቹ በትምህርት ቤት ውስጥ የተለያዩ ፅሁፎችን ማንበብ፣ ከትምህርት ቤት ውጭ ማንበብ፣ የጥቆማ ዘዴዎቻችን በንባብ ጊዜ በአግባቡ መጠቀም፣ እንዲሁም ለብቁ አንባቢነት የሚያበቁ ባህሪያት አውቆ በተግባር ላይ ማዋል ሲሆን በአንብቦ መረዳት ደግሞ ተማሪዎቹ ያነበቡትን ምንባብ እንዲሁ መቀበል ወይም አለመቀበል ሳይሆን ከዚህ በተለየ መልኩ እራስን ስለ አነበቡት ምንባብ መጠየቅን፣ የምንባቡን አጠቃላይና ዝርዝር ሀሳብ መመርመርን፣ ማመዛዘንና ከቀድሞ እውቀት ማመሳከርን የሚጠይቅ ተግባር ነው።

## 2.9 በሀገር ውስጥ የተደረጉ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት

አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማንኛውም የትምህርት መስክ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም። ታዲያ ይህንን አስፈላጊና ጠቃሚ ችሎታ ለማዳበር ያለው አጠቃላይ ጥረት በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ይመስላል ብለን ብንጠይቅ ክሂሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን አንብቦ የመረዳት ችሎታን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፈተሹ ጥናቶች ተስፋዬ (1986)፣ አጥናፍ (1986)፣ ተፈራ (1990) ያመለክታሉ። ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን አንዳንዶቹ በጥናታቸው እንዳመለከቱት ምክንያቱ የንባብ ልምድ ማነስ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ የትምህርት አሰጣጥ ችግር መሆኑን ጠቁመዋል።

ተስፋዬ (1986) ከመሰረቱም ቢሆን የብዙዎቻችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተገቢው መንገድ ባለመዳበሩ የንባብ ልምዳችን ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልፃል። ከዚህም የተነሳ የማንበብ አድማሳችን ጠባብ ነው። ከዚህ አልፎ ያነበብነውን የመገንዘብ ችሎታችንም የምንፈልገውን ያህል ባለመዳበሩ አንብቦ የመገንዘብ ችሎታ (መጠየቅ፣ማመዛዘን፣ መመራመር፣ ማመሳከር) የሚያጠቃልላቸውን ተግባራት የምንፈፅም ብዙዎች አለመሆናችንን አመልክተዋል።

አለማየሁ (1986) እና ጌታቸው (1986) የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱን ይጠቁማሉ። እንደመፍትሄ የሚያቀርቡትም ንባብን በተሻለ ዘዴ ማስተማርና ለንባብ ትምህርት ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ

መሆኑን ነው። በተለይም አለማየሁ (1986) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የተለያየ ይዘቶች ባላቸው ምንባቦች በመጠቀም ንባብን ከፅሕፈት ክሂል በማዛመድ ማለማመድ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ ያመለክታሉ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ጌታቸው (1986)፣ ተስፋዬ(1986)፣ አጥናፍ(1989)፣ አለማየሁ (1986) እና በድሉ(1988) ለንባብ ትምህርት ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ቢያሳስቡም በቀጥታ የንባብ ልምድ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ አላተኮሩም።

ሰለሞን (1990) የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጠናከር የሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎች በተግባር ያለመዋላቸውን፤ በዚህም የተነሳ የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነና በአጠቃላይም የንባብ ባህልን ለማዳበር ልዩ ልዩ ስልቶች አለመቀየሳቸውን ይጠቁማሉ። ሰለሞን አስተያየታቸውን ሲያጠናክሩ አማርኛን በመማር ማስተማር ሂደት ከሚታዩ ችግሮች በተሻለ ውጤት በሚያበቁ ተላምዳዊ ዘዴዎች ማስተማር መሆኑ ዘዴዎቹ በተግባር ማዋል ችግሩን ለማቃለል እንደሚረዳ ይገልፃሉ።

ተፈራ (1990)ም ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት መግቢያ ላይ እንደሚያመለክቱት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው የሚጠበቀውን ያህል አይደለም። ለዚህም ምክንያቱ ትምህርቱ በተገቢው መንገድ ተቀናብሮ ባለመተግበሩ እንደሆነ ገልፅዋል። በጥናቱ ሂደት ባደረጉት የክፍል ክንውን ምልከታ ልምምዱ የሚካሄደው በቃል ንባብ መሆኑን ጠቁመው የሚያነቡትም ተማሪዎች የተወሰኑት እንደሆኑ ያስረዳሉ። በስፋት የሚታየውን ችግር ለመቅረፍም የንባብ ትምህርት የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ተቀናብሮ ተማሪዎቹ ተከታታይ ልምምድ እንዲያደርጉ ያሳስባሉ። ስለዚህም ሰለሞን (1990) እና ተፈራ (1990) እንደሚያብራሩት መምህራኑ ከነባሩ አንብቦ የማስነበብ ዘዴ ተላቀው የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ከሚረዱ መሰረታዊ ሐሳቦች ጋር ተዋውቀው ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የኔሰው (1990) በበኩላቸው በመስተጋብራዊ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል አማካይነት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩትን የማስተማር ችሎታቸውን ለማሻሻል

የሚረዳ መሆኑን በጥናታቸው ማጠቃለያ አመልክተዋል። ብርቱካን (1993) የንባብ ልምድ ከፅሑፈት ክሂል ጋር ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል ለመመርመር ሞክሯል።

ከዚህ በላይ የቀረቡ ጥናቶች (ማስተዋል 1989፣ ተፈራ 1990፣ ሰለሞን 1990) የተማሪዎችንና የመምህራንን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለመገምገም በአማርኛ የንባብ ትምህርት ክፍል ምልከታ አካሂደዋል። በምልከታውም መምህራኑ የሚያዘወትሩት የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ በንበት፣ በመልመጃ ስራዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ የልምምዱ አብዛኛውን ሰዓት የሚሸፈነው በመምህራኑ ስራ በመሆኑ በልምምዱ ሂደት ተማሪዎች የሚኖራቸው ተሳትፎ አናሳ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ይህም ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እየተዳከመ መምጣት የማስተማሪያ ዘዴው የጎላ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የሚያመላክት ነው። በአጠቃላይ የሀገርኛ ጠቋሚ ጥናቶች ለንባብ ትምህርት ልምምድ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልግ ያስምሩበታል። ለማስተማር ደግሞ በተሻለ የማስተማሪያ ዘዴና ወቅታዊ ስልት መጠቀም ተገቢ መሆኑን ሲገልጹ የንባብ ልምድ ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው ተዛምዶ በቀጥታ አልቃኙትም ።

ይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡ ጥናቶች የሚመሳሰለው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ዙሪያ መፈተሹ ሲሆን የሚለይበት ደግሞ በአማርኛ የንባብ ልምድ እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ የሚፈትሽ መሆኑን ነው። በተጨማሪም በክፍል ደረጃ፣ በአካባቢ፣ በተጠኚዎች መጠን፣ በአላማና በጥናቱ ጊዜ ከላይ ከቀረቡ ጥናቶች ይለያል፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የተነሳበትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ከአይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ አንዱ የሆነውን ገላጭ የምርምር ስልት (Descriptive Study) እና በከፊል መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተጠቅሟል። እነዚህ የምርመር ዘዴዎች የተመረጡበት ምክንያት አይነታዊ የምርምር ዘዴ አንድን ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል እንደሆነ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብበት ነው። ችግሩ ምን ይመስላል የሚል ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ሲሆን መጠናዊ የምርምር ዘዴ ደግሞ የችግሩ መጠን ምን ያህል ነው የሚል ጥያቄ ይመልሳል። ጥናቱ በጽሑፍ መጠይቅ፣ በጽሑፍ ፈተና አማካኝነት ስለተማሪዎች የንባብ ልምድ የሚገኘውን መረጃና የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ በማነጻጸር ግንኙነታቸውን ተንትንኖ አቅርቧል።

## 3.1 የናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ከሚገኙ 5 ዞኖች መካከል የምስራቃዊ ዞን በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (Convenience sampling method) ተመርጧል። አካባቢው የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ በአካባቢው በመምህርነት ሙያ በሰራችባቸው ዓመታት ውስጥ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ ውጤት በየዓመቱ ማስመዝገባቸው በአካባቢው ያለው ችግር ምን እንሆነ ለመለየትና የንባብ ልም ዳቸው ከአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ፈትሾ መፍትሔ ለማግኘት ነው።

### 3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በተመረጠው የጥናት አካባቢ ውስጥ 12 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአላማዊ ናሙና አመራረጥ(purposive sampling method) ውቅሮ፣ ነጋሺ፣ዓዲግራት በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል። የተደረገበት ምክንያት ለጥናቱ የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ተቀራራቢ በመሆናቸው ተገቢውን የተጠኚዎች ናሙና በዓይነትም ሆነ በመጠን ማግኘት ይቻላል በማለት ነው።

### 3.1.3 የተጠኚዎች አመራረጥ

ይህ ጥናት በ2003 ዓ.ም በውቅሮ፣በነጋሺ እና በአጉላዕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ10ኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል። በውቅሮ 1200 ተማሪዎች፣ በነጋሽ 480 ተማሪዎች፣ በአጉላዕ 200 ከሚማሩ ተማሪዎች በአጠቃላይ ከ1880 5% በመውሰድ 94 ተማሪዎች በተራ የናሙና አመራረጥ ስልት (Random sampling method) አማካኝነት በተጠኚነት ተመርጠዋል። ከዚህ ተማሪዎች ውስጥ አስር ተማሪዎች በተራ የናሙና አመራረጥ ስልት (Random sampling method) ለሙከራ በተጠኚነት ተመርጠዋል።ለዚህም በመጀመሪያ በእያንዳንዱ በናሙናነት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ምድቦች በትምህርት ቤቱ የተሰጡ መለያ ቁጥሮች (የስም ዝርዝር) ከክፍል ሐላፊ መምህራን የስም መቆጣጠሪያ ላይ በመውሰድ አምስት በመቶ የሚሆነው ተማሪዎች ከስም መቆጣጠሪያ ዝርዝር ላይ የተመዘገቡ ተማሪዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል። አመራረጡም ጠቅላላ ተማሪዎች ተመዝግበው ለእያንዳንዳቸው መለያ ቁጥር ከተሰጣቸው በኋላ ለየግላቸው ተመሳሳይ ቅርጽና መልክ ያላቸው የእጣ ትኬቶች ተዘጋጁ። በተዘጋጁት ትኬቶችም ላይ መለያ ቁጥሮች እየመዘገቡ ትኬቶቹ ተጠቀለሉ። የተጠቀለሉት በደንብ እንዲቀላቀሉ እየተደረገ የተወሰኑ ጥቅሎች በተራ በተራ እየተነሱ ተማሪዎቹ ተመረጡ።

ይህ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተጠኚዎች እኩል የመመረጥ እድል ስለሚሰጥ ነው። እንዲሁም የአንዱ ተጠኚ በናሙናነት መመረጥ በሌላው የመመረጥ እድል ላይ ምንም ተጽእና ስለማያስከትልም ነው።

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጽሑፍ ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል።

### 3.2.1 የጽሑፍ ፈተና

የፈተናው አላማ ተማሪዎች ስለንባብ ልምድ ያላቸውን አጠቃላይ እውቀትና እውቀታቸውን በተግባር የማዋል ብቃታቸውን በማመልከት በተማሪዎችና በአውዶች መካከል ያለውን ግንኙነት የፈተሸ ነው። የጽሑፍ ፈተናው የተዘጋጀው በአጥኚዋ ሲሆን በሶስት ክፍሎች የተከፈሉ 20 ጥያቂዎች የያዘ ነው። ጥያቂዎቹ የክፍትና የምርጫ ጥያቄ የያዙ ናቸው። ፈተናው ተባዝቶ ለተማሪዎቹ ከመሰራጨቱ በፊትም በአማካሪ

እንዲሁም በሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግሞ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተስተካክሎ ለሙከራ ጥናት (Pilot Study) በተመረጡ ተማሪዎች ቀርቦ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ከፈተናው በኋላ መሻሻል ያለበት የፈተና ጥያቄ ተስተካክሎ ለተጠኚዎች ቀርቧል፡፡ ተማሪዎች ጥያቄዎቹን ከመስራታቸው በፊት ምንባቦቹን በጥሞና ማንበብ እንዳለባቸው ተገልጾላቸው፡፡ በተጨማሪም ተፈታኞቹ ፈተናውን በተገቢው መንገድ በጥንቃቄ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ የፈተና ወረቀቶቹ ተሰብስበው በሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአጥኚዋ ታርመዋል፡፡

### 3.2.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ ዓላማ ተማሪዎች ስላላቸው አጠቃላይ የንባብ ልምድ መረጃ ማግኘት ነው፡፡ መጠይቁ 2 ክፍሎች አሉት የመጀመሪያው ክፍል ጥያቄዎች አንድ አይነት የሆኑ አማራጮች ያሉዋቸው አምስት አምስት መመዘኛዎች አሉት፡፡ እነዚህ መመዘኛዎች በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አልስማማም፣ ፍጹም አልስማማም እና መወሰን አልችልም የሚሉ ናቸው፡፡ ክፍል ሁለት የንባብ ልምድን አስመልክቶ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የየራሱ ምርጫዎች የተሰጡትና ክፍት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ቤት ውስጥ የንባብ ልምድ፣ የተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ ያላቸው የንባብ ልምድ፣ ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎትና ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚያሳዩዋቸው ባህሪያት የያዘ ነው፡፡ መጠይቁ ከተዘጋጀ በኋላ በአማካሪ ተገምግሟል፡፡ ከዚያም ለጥናቱ በናሙናት በተመረጡ ተማሪዎች ከመሞላቱ በፊት ግልጽነቱን ለማረጋገጥ ሲባል በተመሳሳይ የክፍል ደረጃዎች ከሚገኙ ተማሪዎች 10 የሚሆኑ ተመርጠው መጠይቁን እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ በመቀጠል መሻሻል የሚገባውን መጠይቅ ማለት ግልጽነት ያልነበራቸውን በግልጽ በማቅረብ አስፈላጊ ያልሆኑትን በማስወገድና በማስተካከል ለናሙናነት በተመረጡ 120 ተማሪዎች ተሰጥቶ እንዲሞሉት በማድረግ የ94ቱ ተማሪዎች መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት የተካሄደው የመረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ በተለያዩ ቀመሮች (አማካይ ውጤትን፣መደበኛ ልይይት፣ የተዛምዶ ስሌትን እና T-Test) እና ስሌቶችን በመረጃ መተንተኛነት በመጠቀም ነው፡፡ ተማሪዎቹ ያላቸውን የማንበብ እውቀትና

እውቀታቸውን በተግባር የማዋል ብቃት ለመተንተን የመቶኛ ስሌት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎች የማንበብ ልምድ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ መቶኛን በመጠቀም ነው፡፡ በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ለማወቅ ደግሞ አማካይ ውጤትን፣ መደበኛ ልይይትን፣ የተዛምዶ ስሌትን እና T-Test የሚባሉትን በመረጃ መተንተኛነት ተገልግሏል፡፡ በመረጃ አተናተን ሂደትም በመጀመሪያ ስለተማሪዎቹ የንባብ ልምድ በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአራት ክፍሎች በመመደብ ምድባቸው ከተደራጁ በኋላ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየታዩ በመቶኛ ተተንትነዋል፡፡ ተማሪዎች ስላላቸው የንባብ እውቀትና እውቀታቸውን በተግባር የማዋል ብቃት ለመፈተሽ በተማሪዎች የተሰራ ሙከራ በማረም፣ ከታረሙ በኋላ የተገኘው አማካይ ውጤት ተወስዷል፡፡ ከሙከራው የተገኘው ውጤትም አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ በፈተና ጥያቄዎች አስቸጋሪነት መለኪያ (index of items difficulty) እና በፈተና ጥያቄዎች የመመዘን ብቃት መለኪያ (Index of item discrimination power) ተፈትሸዋል፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ በፈተና ያገኙት ውጤት በመቶኛ እየተሰላ ብቃታቸው ዝቅተኛ፣ መካከለኛ ወይም ከፍተኛ መሆኑ ተለይቷል፡፡

በመቀጠልም አጠቃላይ የተማሪዎች የንባብ ልምድ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ ከዚህም ስሌት በመነሳት ከንባብ ልምድ አንጻር በተማሪዎች መካከል የሚታየው ልዩነት ተተንትኗል፡፡ ከዚያም የተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መካከል ያለው ግንኙነት ለማወቅ የሁለቱን ውጤት በተዛምዶ ስሌት(correlation coefficient) መለካት በማስፈለጉ ቀመሩ ተመርጧል፡፡ ስለዚህም ግንኙነት መኖር ወይም አለመኖሩን በማረጋገጥ(Person product movement correlation coefficient) የቀመሩ ስሌት (Row score) ቀመር ግንኙነት ተፈትሿል፡፡

በመጨረሻም በተዛምዶ ስሌት ተሰርቶ የተገኘው ውጤት ከስህተት ነፃ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በአስተማማኝነት የግንኙነት መለኪያ ስሌት በ t-test ቀመር ተፈትሿል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

ለጥናቱ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን ረገድ በቅድሚያ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ ስላላቸው የንባብ ልምድ፣ የተማሪዎቹ የንባብ ፍላጎትና በሚያነቡበት ጊዜ የሚያሳዩአቸውን ባህሪያት እንዲሁም ተማሪዎቹ ስላላቸው የንባብ ችሎታና ችሎታቸውን በተግባር የማዋል ብቃት ለመፈተሽ ከቀረበው መጠይቅ የተገኙት ውጤቶች በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል። በመጨረሻም በተማሪዎች የንባብ ልምድና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ዝምድና ለማወቅ ደግሞ አማካይ ውጤትን፣ መደበኛ ልይይትን፣ የተዛምዶ ስሌትን እና t-test ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ትንታኔ ቀርቧል።

#### 4.1.1 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**ክፍል አንድ**

**ሠንጠረዥ 2፡-** በየትምህርት ቤቱ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ ተማሪዎችን ብዛት የሚያሳይ መረጃ

| ት/ቤት | | ፆታ | | ድምር | ዕድሜ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | | 13-15 | 16-18 | |
| ውቅሮ | ብ | 32 | 28 | 60 | 20 | 40 | 60 |
| | % | 34 | 29.7 | 63.8 | 21.2 | 42.5 | 63.8 |
| ነጋሽ | ብ | 10 | 14 | 24 | 15 | 9 | 24 |
| | % | 10.6 | 14.8 | 25.5 | 15.9 | 9.5 | 25.5 |
| አጉላዕ | ብ | 4 | 6 | 10 | 3 | 7 | 10 |
| | % | 4.2 | 6.3 | 10.6 | 3.1 | 7.4 | 10.6 |
| ድምር | ብ | 46 | 48 | 94 | 38 | 56 | 94 |
| | % | 48.9 | 51 | 100 | 40.4 | 59.5 | 100 |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት 94 ተማሪዎች ውስጥ 63.8% ከውቅሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ 25.5% ከነጋሽ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆኑ 10.6% ከአጉላዕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው። በ3ቱ ትምህርት ቤት ካሉ ተማሪዎች ውስጥ ወንድ ተማሪዎች 48.9% ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ 51% ናቸው። እንዲሁም ከ13-15 የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ 40.4% ሲሆኑ ከ16-18 59.5% ናቸው።

የተማሪዎች የትምህርት ቤት ውስጥ የንባብ ልምድ ከቀረበው መጥይቅ የተገኙ መረጃዎች፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡- በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ የተገኙ መረጃዎች**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጭ መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፍፁም አልስማማም | | መወሰን አልችል | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 5 | መጻሕፉትን ለማንበብ ከቤተ መጻሕፍት ተውሼ አላውቅም | 20 | 21.2 | 28 | 29.7 | 26 | 27.6 | 13 | 13.8 | 7 | 7.4 |
| 8 | አዘውትሬ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ በመግባት አነባለሁ | 13 | 13.8 | 11 | 11.7 | 34 | 36.1 | 31 | 32.9 | 5 | 5.3 |

በሠንጠረዡ ከቀረብ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት 94 ተማሪዎች መካከል መጻሕፍትን ለማንበብ ከቤተመጻሕፍት ተውሼ ኣላውቅም ለሚለው ጥያቄ 21.2% በጣም እስማማለሁ፣ 29.7 % የሚሆኑትትኑትን እስማማለሁ፣ 27.6 % የሚሆኑት አልስማማም፣ 13.8% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም የሚል ምላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 7.4 % የሚሆኑት መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከቤተመጻሕፍት መጻሕፍትን በመዋስ እንደማያነቡ አመልካች ነው፡፡ በተጨማሪ ከክፍት ጥያቄ ተ.ቁ 5 በአንድ ርዕስ ላይ መረጃ ሰብስበህ/ሽ አጭር ጽሑፍ እንድታቀርብ/ቢ ብትታዘዝ/ዢ መረጃ ከየት ታገኛለህ/ሽ ለሚለው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሰው እጠይቃለሁ የሚል መልስ ሲሰጡ አናሳው ደግሞ ከቤተመጻሕፍት አስፈላጊ መጻሕፍት እፈልጋለሁ ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም ልምድ አለመኖራቸው የሰጡት ምላሽ አመልካች ነው፡፡ ይህም ከሠንጠረዥ 3 ተ.ቁ 5 እና 8 ከሰጡት ምላሽ ጋር ይዛመዳል፡፡ አዘውትሬ ቤተመጻሕፍት ውስጥ በመግባት አነባለሁ ለሚለው ጥያቄ 13.8 % የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም እስማማሁ፣ 11.7% የሚሆኑት ደግሞ እስማማሁ፣ 36.1% የሚሆኑትን አልስማማም፣ 32.9% ፍጹም አልስማማም የሚል ምላሽ ሲሰጡ

5.3% የሚሆኑት ደግሞ መወሰን አልችልም ብለዋል፡፡ ስለዚህ አዘውትሬ በቤተመጻሕፍት በመግባት አነባለሁ ተብሎ ለቀረበው ሃሳብ ከተሰጠው ምላሽ ውጤትም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ባለው ቤተመጻሕፍት መጠቀም እንደማይፈልጉ ከውጤቱ መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ የተማሪዎች ምላሾች እንደሚያሳዩት ከቤተመጻሕፍት መጻሕፍትን የመዋስ ልምድ የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ቤተመጻሕፍት አዘውትረው በመግባት እንደማያነቡ ውጤቱ ያመለክታል፡፡ እንዲሁም ከክፍት ጥያቄ ተ.ቁ 1 መጽሐፍ ማንበብ ትወዳለህ/ሽ? ለሚለው ጥያቄ እና ለተ.ቁ 2 የእረፍት ጊዜህን/ሽን የምታሳልፈው/ፊው በምን መልኩ ነው ለሚለው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ ውጤትም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች መጻሕፍ ከማንበብ ይልቅ ሌላ ሥራ መስራት እንደሚወዱ ገልጸዋል፡፡ ይህም ከሠንጠረዥ 3 ተ.ቁ 5 እና 8 ከቀረበው ውጤት ጋር ይስማማል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ለማጎልበት በመምህራ የሚደረገውን እገዛ በተማሪዎች እይታ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጭ መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፍፁም አልስማማም | | መወሰን አልችልም | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 9 | መምህራን በክፍል ውስጥ ምንባብ ሲያስነብቡን እንዴት ማንበብ እንዳለብን | 33 | 35.1 | 44 | 46.8 | 8 | 8.5 | 6 | 6.3 | 3 | 3.1 |
| 10 | መምህራን በክፍል ውስጥ በአብዛኛው በግል የለሆሳስ ስልት ያስነብቡኛል፡፡ | 9 | 9.5 | 46 | 48.9 | 20 | 21.2 | 11 | 11.7 | 8 | 8.5 |
| 11 | መምህራን የተለያዩ ለንባብ የሚሆኑ መፃህፍትን እየጠቆሙኝ አነባለሁ፡፡ | 14 | 14.8 | 27 | 28.7 | 41 | 43.6 | 8 | 8.5 | 4 | 4.2 |

በሠንጠረዥ 4 እንደሚታየው በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ለማጎልበት በመምህራን የሚደረገውን እገዛ ለማወቅ ለቀረቡት 3 ጥያቄዎች መምህራን በክፍል

ውስጥ ምንባብን ሲያስነብቡ እንዴት ማንበብ እንዳለብኝ ያስረዱኛል ብሎ ለቀረበው ጥያቄ 35.1% በጣም እስማማለሁ፣ 46.8% እስማማለሁ፣ 8.5% አልስማማም፣ 6.3% ፍፁም አልስማማም የሚል ምላሽ ሲሆን 3.1% ደግሞ መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል። መምህራን በክፍል ውስጥ በአብዛኛው በግል የለሆሳስ ስልት ያስነብቡኛል ለሚለው ጥያቄም 9.5% በጣም እስማማለሁ፣ 48.9% እስማማለሁ 21.2% አልስማማም፣ 11.7 ፍጹም አልስማማም ፣ 8.5 መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። መምህራን የተለያዩ ለንባብ የሚሆኑ መጻሕፍትን እየጠቆሙኝ አነባለሁ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 14.8% በጣም እስማማለሁ፣ 28.7% እስማማለሁ 43.6% አልስማማም፣ 8.5 ፍጹም አልስማማም፣ 4.2 መወሰን አልችልም በማለት መልሰዋል።

የሠንጠረዥ 4 ጥያቄ (ቁጥር 9 እና 10) ምላሾች እንደሚያሳዩት የተማሪዎችን የንባብ ልምድ ለማሻሻል በትምህርት ቤት ውስጥ መምህራን እገዛ የሚያደርጉ ሆነው ተገኝተዋል። እንዲሁም በክፍት ጥያቄ ተ.ቁ 4 አስተማሪህ/ሽ በክፍል ውስጥ ለንባብ ልምድ የሚያደርግልህ/ሽ እገዛ ተገቢ ነው ትላለህ/ያለሽ? አዎ ከሆነ መልስህ/ሽ እንዴት? ለሚለው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ አዎ የሚል ሲሆን ምክንያታቸውም አስተማሪያችን በክፍል ውስጥ የተለያየ ዘዴ በመጠቀም ንባብ እንድንለማመድና ፍላጎት እንዲኖረን ጥረት ያደርጋሉ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም ውጤት ከሠንጠረዥ 4 ጥያቄ ተ.ቁ 10 እና 9 ከተሰጠው ምላሽ ይስማማል። ይሁን እንጂ በሠንጠረዥ ሁለት ጥያቄ ቁጥር 11 ከተሰጠው ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህራን ለተማሪዎቻቸው የንባብ ልምድን መሻሻል አጋዥ የሆኑ ጽሑፎችን እንዲያነቡ የሚሰጡት ድጋፍና ጥቆማ አነሳ ሆኖ ተገኝቷል።

ሰንጠረዥ 5፦ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ ያላቸው የንባብ ልምድ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጭ መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፍፁም አልስማማ | | መወሰን አልችልም | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 2 | አልፎ አልፎ መፃሕፍትን በመግዛት አነባለሁ፡፡ | 30 | 31.9 | 42 | 44.6 | 11 | 11.7 | 3 | 3.1 | 8 | 8.5 |
| 3 | በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ በርካታ መጻሕፍት ስላሉ አነባለሁ፡፡ | 6 | 6.3 | 20 | 21.2 | 33 | 35.1 | 25 | 26.5 | 10 | 10.6 |
| 13 | ቤተሰቦቼ የማነባቸውን መጻሕፍት ገዝተውም ሆነ ተውሰው ይሰጡኛል፡፡ | 9 | 9.5 | 21 | 22.3 | 37 | 39.3 | 22 | 23.4 | 5 | 5.3 |

በሰንጠረዥ 5 እንደሚታየው አልፎ አልፎ መጻሕፍት በመግዛት አነባለሁ የሚለውን ጥያቄ ከመለሱት ተማሪዎች ውስጥ 31.9% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ፣44.6%የሚሆኑት እስማማለሁ፣ 11.7% የሚሆኑት አልስማማም፣ 3.1% ፍፁም አልስማማም፣ ቀሪዎቹ 8.5% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ውጤቱም በቁጥር በርካታ የሆኑት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ የማንበብ ልምዳቸው ዝቅተኛ መሆንና በአብዛኛው መጻሕፍት በግላቸው ገዝተው እንዲሁም በአቅራቢያቸው አግኝተው እንደማያነቡ ከውጤቱ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ በርካታ መጻሕፍት ስላሉ አነባለሁ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ 6.3% በጣም እስማማለሁ፣ 21.2% እስማማለሁ፣ 35.1% አልስማማም፣ 26.5% ፍጹም አልስማማም፣ 10.6% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በቁጥር በርካታ የሆኑት ተማሪዎች በመኖሪያ ቤታቸው መጻሕፍት እንደማያገኙ መረጃው ይጠቁማል፡፡ ከዚህ መጠይቅ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች መጻሕፍት የማግኘት እድላቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ከክፍት ጥያቄ ተ.ቁ 3 በትምህርት ቤትህ/ሽ ወይም በቤትህ/ሽ ንባብን እንዳትለማመድ/ጂ የሚያደርግህ/ሽ ነገር ግለፅ/ጪ ለሚለው ሃሳብ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ አንብቦ ለመረዳት ችግር እንዳለባቸውና በጊዜ ማነስ ምክንያት ማንበብ እንዳልቻሉ ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ይህም ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸውን ሊያጎለብቱ እንዳልቻሉ

ከውጤቱ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ሃሳብ ደግሞ ከሠንጠረዥ 5 ተ.ቁ 2 እና 3 በእጅጉ ይዛመዳል፡፡

ቤተሰቦቼ የማነባቸውን መጻሕፍት ገዝተው ሆነ ተውሰው ይሰጡኛል የሚለው ጥያቄ 9.5% በጣም እስማማለሁ፣ 22.3% እስማማለሁ፣ 39.3% አልስማማም፣ 23.4% ፍጹም አልስማማም፣ 5.3% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ውጤቱ እንደሚያሳየው ተማሪዎች ልምዳቸው እንዲጎለበት በወላጆቻቸው የሚደረገውን ጥረት ዝቅተኛ ሆኖ  ተገኝቷል፡፡

የሠንጠረዥ 5 ጥያቄ ተራ ቁጥር 2፣3፣13 ምላሾች እንደሚያሳዩት በቁጥር በርካታ የሆኑት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ መጻሕፍትን በግላቸው ገዝተው ሆነ በአቅራቢያቸው አግኝተው የመጠቀም እድላቸው አናሳ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎችን የንባብ ልምድ የሚያጎለብቱበት ሁኔታዎች ያልተመቻቹላቸው መሆኑን ከውጤቱ መረዳት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡- የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጭ መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፍፁም አልስማማም | | መወሰን አልችልም | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1 | ከምንም ነገር በላይ መጻሕፍትን ማንበብ እወዳለሁ | 51 | 54.2 | 37 | 39.3 | 3 | 3.1 | 1 | 1.06 | 2 | 2.1 |
| 4 | መጻሕፍትን ከማንበብ ይልቅ ሌላ ስራ መስራት እመርጣለሁ | 7 | 7.4 | 9 | 9.5 | 35 | 37.2 | 35 | 37.2 | 8 | 8.5 |
| 6 | መጻሕፍትን እንዳነብ ካልታዘዝኩ በስተቀር የማነበው አልፎ አልፎ ነው | 4 | 4.2 | 17 | 18 | 31 | 32.9 | 40 | 42.5 | 2 | 2.1 |
| 7 | ሰዎች በነገሩኝ አንድ ሃሳብ ላይ ተጨማሪ እውቀት ለማግኘትመጻሕፍትን አላነብም | 4 | 4.2 | 9 | 9.5 | 26 | 27.6 | 47 | 50 | 8 | 8.5 |
| 12 | የማንበብ ፍላጎትያሳደሩብኝ የማደንቃቸው አንባቢዎች በአካባቢዬ አጋጥመውኛል፡፡ | 13 | 13.8 | 41 | 43.6 | 15 | 15.9 | 13 | 13.8 | 12 | 12.7 |

በሰንጠረዥ 6 እንደተገለጸው ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ፍላጎት ለማወቅ ታስቦ ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ከምንም ነገር በላይ መጻሕፍትን ማንበብ እወዳለሁ ለሚለው ጥያቄ 54.2% በጣም እስማማለሁ፣ 39.3% እስማማለሁ፣ 3.1% አልስማማም፣ 1.06% ፍጹም አልስማማም፣ 2.1% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ መጻሕፍትን ከማንበብ ይልቅ ሌላ ስራ መስራት እመርጣለሁ ለሚለው ነጥብም 7.4% በጣም እስማማለሁ፣ 9.5% እስማማለሁ፣ 37.2% አልስማማም፣ 37.2% ፍጹም አልስማማም፣ 8.5% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ መጻሕፍትን እንዳነብ ካልታዘዝኩ በስተቀር የማነበው አልፎ አልፎ ነው ለሚለው ነጥብም 4.2% በጣም እስማማለሁ፣ 18% እስማማለሁ፣ 32.9% አልስማማም፣ 42.5% ፍጹም አልስማማም፣ 2.1% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ሰዎች በነገሩኝ አንድ ሐሳብ ላይ ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት መጻሕፍት አላነብም የሚለው ነጥብም 4.2% በጣም እስማማለሁ፣ 9.5% እስማማለሁ፣ 27.6% አልስማማም፣ 50% ፍጹም አልስማማም፣ 8.5% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የማንበብ ፍላጎት ያደረብኝ የማደንቃቸው አንባቢዎች በአካባቢዬ ስለአጋጠሙኝ ነው ለሚለው ሐሳብም 13.8% በጣም እስማማለሁ፣ 43.6% እስማማለሁ፣ 15.9% አልስማማም፣ 13.8% ፍጹም አልስማማም፣ 12.7% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ከተገኘው ምላሽ በቁጥር በርካታ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ ጥሩ የንባብ ልምድ ለማጎልበት እንደቻሉ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

የሠንጠረዥ 6 ጥያቄ ተራቁጥር 1፣4፣6፣7፣12 ምላሾች እንደሚያመለክቱት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቁጥር በርካታ የሆኑ ተማሪዎች ጥሩ የማንበብ ፍላጎት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 7፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚያሳዩአቸው ባህሪያት

| ተ.ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | አማራጭ መልሶች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ፍፁም አልስማማም | | መወሰን አልችልም | |
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 14 | አንድ ፅሑፍ ሳነብ መልእክቱን ለመገምገም ጥረት አላደርግም | 44 | 46.8 | 40 | 42.5 | 3 | 3.1 | 2 | 2.1 | 5 | 5.3 |
| 15 | አንድ መጽሐፍ ሳነብ መልእክቱ ካልገባኝ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለመረዳት እሞክራለሁ፡፡ | 2 | 2.1 | 2 | 2.1 | 53 | 56.3 | 34 | 36.1 | 3 | 3.1 |
| 16 | በማነበው ጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ ስህተቶች ሲያጋጥሙኝ በማስተካከል አነባለሁ፡፡ | 41 | 43.6 | 47 | 50 | 4 | 4.2 | 1 | 1.06 | 1 | 1.06 |
| 17 | አንድ ጽሑፍ ሳነብ ከፀሐፊው ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቼ የማወያየት ስሜት ይሰማኛል፡፡ | 27 | 28.7 | 12 | 12.7 | 41 | 43.6 | 6 | 6.3 | 8 | 8.5 |
| 18 | በማነብበት ጊዜ በእያንዳንዱ እይታዬ የአንድ ነጠላ ቃልን በመቃኘት አነባለሁ | 10 | 10.6 | 44 | 46.8 | 24 | 25.5 | 9 | 9.5 | 8 | 8.5 |
| 19 | በማነብበት ጊዜ በጣቴ ወይም በሹል ነገር መጠቆም እወዳለሁ | 24 | 25.5 | 27 | 28.7 | 26 | 27.6 | 9 | 9.5 | 8 | 8.5 |
| 20 | አንድን ጽሑፍ ሳነብ መልእክቱ ካልገባኝ ጽሑፉን ቃል በቃል ለመሸምደድ እሞክራለሁ፡፡ | 32 | 34 | 32 | 34 | 14 | 14.8 | 8 | 8.5 | 8 | 8.5 |

በሰንጠረዥ 7 ከተራ ቁጥር 15 እስከ ተራ ቁጥር 17 የቀረቡት ጥያቄዎች የብቁ አንባቢዎችን ባህሪ የሚገልፁ ናቸው፡፡ የእያንዳንዱ ነጥብ ምላሽ ሲታይ አንድን ጽሑፍ ሳነብ መልእክቱን ለመገምገም ጥረት አላደርግም ለሚለው ጥያቄ ከሞሉት 94 ተማሪዎች ውስጥ 46.8% በጣም እስማማለሁ፣42.5% እስማማለሁ፣ 3.1% አልስማማም፣2.1% ፍጹም አልስማማም፣ 5.3% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አንድን ጽሑፍ ሳነብ መልእክቱ ካልገባኝ የተለያዩ ስልቶች በመጠቀም

ለመረዳት እሞክራለሁ የሚለው ደግሞ 2.1% በጣም እስማማለሁ፣2.1% እስማማለሁ፣ 56.3% አልስማማም፣ 36.1% ፍጹም አልስማማም፣ 3.1% መወሰን አልችልም በማለት መልሰዋል። በማነበው ጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ ስህተቶች ሲያጋጥሙኝ በማስተካከል አነባለሁ ለሚለው መጠይቅም 43.6% በጣም እስማማለሁ፣ 50% እስማማለሁ፣ 4.2% አልስማማም፣1% ፍጹም አልስማማም፣1% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል። አንድን ጽሑፍ ሳነብ ከጸሐፊው ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቼ የመወያየት ስሜት ይሰማኛል የሚለው ነጥብም 28.7% በጣም እስማማለሁ፣12.7% እስማማለሁ፣ 43.6% አልስማማም፣ 6.3% ፍጹም አልስማማም፣ 8.5% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል።

በሰንጠረዥ 7 በተራ ቁጥር 14፣18፣19፣20 የቀረቡት ጥያቄዎች ደግሞ ብቁ ያልሆኑ አንባቢዎች ባህሪያት የሚገልጹ ናቸው። ለጥያቄዎቹ የተሰጡት ምላሾች ሲታዩ በማነብበት ጊዜም በእያንዳንዱ እይታዬ አንድ ነጠላ ቃልን በመቃኘት አነባለሁ ለሚለው ጥያቄ 10.6% በጣም እስማማለሁ፣46.8% እስማማለሁ፣ 25.5% አልስማማም፣ 9.5% ፍጹም አልስማማም፣ 8.5% መወሰን አልችልም የሚል መልስ ሰጥተዋል። በማነብበት ጊዜ በጣቴ ወይም በሹል ነገር መጠቆም እወዳለሁ ለሚለው ሀሳብ 25.5% በጣም እስማማለሁ፣ 26.7% እስማማለሁ፣ 27.6% አልስማማም፣ 9.5% ፍጹም አልስማማም፣ 8.5% መወሰን አልችልም በማለት መልሰዋል። አንድን ጽሑፍ ሳነብ መልእክቱ ካልገባኝ ጽሑፉን ቃል በቃል ለመሸምደድ እሞክራለሁ ለሚለው ነጥብ ደግሞ 34% በጣም እስማማለሁ፣34% እስማማለሁ፣ 14.8% አልስማማም፣ 8.5% ፍጹም አልስማማም፣ 8.5% መወሰን አልችልም የሚል ምላሽ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ በሠንጠረዥ 7 ከቀረቡት 7 ጥያቄዎች መካከል በተራ ቁጥር 14፣ 15፣ 17፣ 18፣19፣20 ለእያንዳንዳቸው ከተሰጡት ምላሾች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የብቁ አንባብያን ባህሪያት እንደማያሟሉ የተገኘው ውጤት ያሳያል። ነገር ግን በተራ ቁጥር 16 የሰጡት ምላሽ አብዛኞቹ ተማሪዎች እስማማለሁ የሚል ነው።

## ክፍል ሁለት

### 4.1.2 ከክፍል ሁለት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 8 ፦ የማንበብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች ከቤተ መጻሕፍት ጋር ያላቸውን ቁርኝት አስመለክቶ የተገኙ መረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1. | “ወደ ቤተ መጻሕፍት ምን ያህል ጊዜ ትሄዳለህ/ሽ”? | | |
| | ሀ. በየቀኑ | | 15.9 |
| | ለ. በየሳምንቱ | 15 | 11.7 |
| | ሐ. በየወሩ | 11 | 61.7 |
| 2. | የምታነቧቸውን መጻሕፍት የምታገኙዋቸው በምን ዓይነት መንገድ ነው? | | |
| | ሀ. በግዢ | 14 | 14.89 |
| | ለ. ከቤተ መጻሕፍት በመዋስ | 7 | 7.4 |
| | ሐ. ከዘመድ ወዳጅ | 60 | 63.8 |
| | መ. አላነብም | 12 | 12.7 |
| 3 | በአንተ/አንቺ ግምት የንባብ ልምድህ/ሽ ምን ያህል ነው? | | |
| | ሀ. ከፍተኛ | 18 | 19.14 |
| | ለ. መካከለኛ | 52 | 55.3 |
| | ሐ. ዝቅተኛ | 24 | 25.5 |

ከሠንጠረዥ 8 ተራቁጥር 1 እንደምረዳው “ወደ ቤተመጻሕፍት ምን ያህል ጊዜ ትሄዳለህ/ሽ የሚለው ጥያቄ 15.9% በየቀኑ፣ 11.7% በየሳምንቱ፣ 61.7% በየወሩ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል ከጥያቄው ምላሽ የምንረዳው ተማሪዎች ሁልጊዜ ወደቤተመጻሕፍት እንደማይሄዱ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች የንባብ ልምድ የሚኖራቸው በየጊዜው ወደ ቤተመጻሕፍት በመግባት መጻሕፍትን ማንበብ ከቻሉ ነው።

ከሠንጠረዥ 8 ተ.ቁ 2 የምታነቧቸውን መጻሕፍት የምታገኙዋቸው በምን ዓይነት መንገድ ነው? የሚለው ጥያቄ14.8% በግዢ፣ 7.4% ከቤተመጻሕፍት በመዋስ፣ 63.8% ከዘመድ ወዳጅ የሚሉ ሲሆኑ 12.7% ደግሞ አላነብም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

በአንተ/አንቺ ግምት የንባብ ልምድህ/ሽ ምን ያህል ነው? ለሚለው ሃሳብ 19.14% ከፍተኛ፣ 55.3% መካከለኛ 25.5% ዝቅተኛ የሚል መልስ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ ከዚህ መጠይቅ የምንረዳው ብዙዎቹ ተማሪዎች በቤተመጻሕፍት የማንበብ ልምድ እና ለንባብ ልምድ ያላቸው ግምት የሚያመረቃ አይደለም። ከመጻሕፍት ጋርም ያላቸው ትስስር በጣም የላላ ነው። ሆኖም ግን የንባብ ልምድ የሚዳብረው መጻሕፍት በየጊዜው በማንበብና ለንባብ ያለን ግምት ከፍተኛ መሆኑን ባለሙያዎች (ለምሳሌ፡- አለም 2001) ያስረዳሉ።

ሰንጠረዥ: 9. ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ችሎታ በተግባር የማዋል ብቃት ለመገምገም ከተሰጡት ፈተናዎች የተገኙ መረጃዎች

| የተማሪዎች ብዛት | | በፈተናው ያገኙት ውጤት በመቶኛ |
|---|---|---|
| በቁጥር | በመቶኛ | |
| 63 | 67% | ከ 60% በታች |
| 24 | 25.5% | ከ61-70% |
| 7 | 7.4% | ከ71-90% |

ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ችሎታ በተግባር የማዋል ብቃት ለማወቅ 20 ጥያቄዎችን የያዘ ፈተና ቀርቦላቸው ነበር። በፈተናውም ከ94 ተማሪዎች ውስጥ 67% የሚሆኑት እያንዳንዳቸው ያስመዘገቡት ውጤት ከ60 በታች ነው። እንዲሁም 25.5% የሚሆኑት በፈተናው እያንዳንዳቸ ከ61-70% የሚሆን ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆኑ 7.4% የሚሆኑ ተማሪዎች ከ 71-90 የሚሆን ውጤት አስመዝግበዋል። ይህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ባላቸው የንባብ ልምድ ያጎለበቱትን የማንበብ ችሎታ በተግባር ላይ ለማዋል ያላቸው ብቃት ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል።

ሰንጠረዥ፡ 10. የተማሪዎች የንባብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ

| ተነፃፃሪዎች | Mean (x) | sd | r | df | tb | tcv |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪዎች የንባብ ልምድ ውጤት | 62.1 | 8.27 | 0.66 | 93 | 8.37 | 0.232 |
| የአማርኛ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ (ውጤት) | 56.6 | 7.07 | | | | |

$P < 0.05$

በሰንጠረዥ 10 እንደሚታየው የተማሪዎች የንባብ ልምድ አማካይ ውጤት 62.1 ሲሆን የአማርኛ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ደግሞ 56.6 ነው፡፡ እንዲሁም ከተማሪዎቹ የንባብ ልምድ የተገኘው መደበኛ ልይይት /SD/ 8.27 ሲሆን የአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤታቸው መደበኛ ልይይት ደግሞ 7.07 ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ልይይቶች ሲታዩ አነስተኛ አሃዞች ናቸው፡፡ ይህም የእያንዳንዱ ተማሪ የንባብ ልምድ ውጤትም ሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ከተገኙት አማካይ ውጤቶች ብዙም የራቁ አለመሆናቸውን ያመለክታል፡፡ የተማሪዎቹ የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት መካከል ግንኙነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በሁለቱ መካከል ያለው የተዛምዶ ስሌት ውጤት (r) ተሰልቶ ስሌቱም 0.66 ሆኗል፡፡ ይህም አሃዝ ትልቅ አዎንታዊ ቁጥር በመሆኑ በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት መካከል የጠነከረ ግንኙነት መኖሩን ያመለክታል፡፡

በተማሪዎቹ የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ መረዳት ውጤት መካከል የታየው ይህ ጠንካራ ግንኙነት ከስህተት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በተሰራው የአስተማማኝ ግንኙነት መለኪያ ስሌት የ t-test ቀመር 8.37 ውጤት ተገኝቷል፡፡ ይህ በምናልባት ስህተት 5% ላይ ከተመዘገበው (tcv) 0.232 ዋጋ በልጧል፡፡ በዚህም በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል የታየው ጥሩ ተዛምዶ አስተማማኝ ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ውስጥ ጥሩ የማንበብ ልምድ ያለው ተማሪ በአንብቦ የመረዳት ችሎታው ከፍተኛ እንደሚሆን ተገልጿል፡፡ ከጥናቱ ውጤት የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተውም ተጠኚዎቹ ተማሪዎች የማንበብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሌላቸው ነው፡፡ ይህም የንባብ ልምድ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያመለክታል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በዚህ ጥናት የተማሪዎቹን የንባብ ልምድ በትምህርት ቤት ውስጥ ለማጎልበት የተደረገውን ጥረት ለማወቅ በተካሄደው ጥናት የተማሪዎቹ የንባብ ልምድ እንዲያጎለብቱ መምህራን በክፍል ውስጥሲያስተምሩ ተማሪዎቹ ማንበብን እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው እንደሚነግሯቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ ይህም Silberstein (1994) በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት በተራ ቁጥር 2.3 እንደተገለጸው ተማሪዎቹ አግባብነት ያለው የአነባበብ ስልት እየመረጡ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን እንዲያነቡ ማድረግ ልምዳቸውን ለማጎልበት ያግዛቸዋል በማለት ካቀረቡት ሀሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡ ከዚህም ሌላ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በአብዛኛው በግል የለሆሳስ ንባብ ስልት ማስነበብ የሁሉንም ተማሪዎች የንባብ ልምድ በተመጣጣኝ ደረጃ ለማሳደግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል በማለት ከገለፁት ሀሳብ ጋር ይስማማል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን በየጊዜው የተለያዩ የንባብ መጻሕፍትን እየጠቆሙ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጭ እንዲያነቡ አለማድረጋቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም ከክፍል ውጭ ለሚከናወኑ የንባብ ተግባራት መምህራን የሚሰጡት ድጋፍ አናሳ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የተገኘው የጥናቱ ተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት በተራ ቁጥር 2.3.1 እንደተገለጸው Arcy (1973) መምህራን በትምህርት ቤቱ የሚያገኙ አጋዥ የንባብ መጻሕፍት የሚገኙበትንና የሚገዙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል በማለት ካቀረቡት ሀሳብ ጋር በእጅጉ ይቃረናል፡፡

በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኘው ቤተ መጻሕፍት ገብተው መጻሕፍትን በማንበብ የንባብ ልምዳቸውን ለማጎልበት የሚያደርጉት ጥረት ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ይህም ውጤት በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.3.1 ላይ Key (1977) "የተማሪዎች የንባብ ልምድ ይበልጥ የሚጎለብተው አዘውትረው በቤተ መጻሕፍት የመጠቀም ልምድ ሲኖራቸው ነው" በማለት ካቀረቡት አስተያየት ጋር ይቃረናል፡፡ ስለዚህ መምህራኑ ያደረጉት ጥረት በክፍል ውስጥ የተገደበ መሆኑን እና ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ለሚያደርጉት የንባብ ልምምድ የሚሰጡት ጥቆማ አናሳ መሆኑን ውጤቱ ያሳያል፡፡

የተማሪዎች የንባብ ልምድ ከሚጎለብትበት ዘዴ አንዱ ከትምህርት ቤት ውጭ በሚያደርጉት የንባብ ልምምድ ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከትምህርት

ቤት ውጭ ወላጆቻቸው መጻሕፍት ገዝተውም ሆነ ተውሰው እንደማይሰጧቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት በተራ ቁጥር በ 2.3.1 እንደተገለጸው Chubby (1991) የተማሪዎች የንባብ ልምድ ለማጎልበት ወላጆች የተለያዩ መጻሕፍትን ለልጆቻቸው እያቀረቡ እንዲያነቡ ማገዝ አለባቸው በማለት ከገለፁት ሃሳብ ጋር ይቀረናል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ በቤታቸው መጻሕፍት አለመጠቀማቸው ለወደፊት የንባብ ልምዳቸው ይበልጥ እንዳይጎለብት መሰናክል ሊሆን ይችላል፡፡

ተማሪዎች በአካባቢያቸው ጥሩ የሆኑ አንባቢዎችን ካገኙ ለማንበብ ፍላጎታቸው ተነሳስቶ የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብ የንባብ ልምዳቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በሞዴልነት የሚያዩት ወይም የሚያገኙት አንባቢ እንዳለ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም ውጤት በምዕራፍ ሁለት በተ.ቁ 2.3.2 እንደተገለጸው May(1990) "ጥሩ የንባብ ልምድ እንዲኖራቸው የሚፈ ልጉ ልጆች ማንበብን የሚወዱና የሚያነቡ ሞዴል አንባቢዎች ባካባቢያቸው ሊኖራቸው ይገባል" በማለት የሞዴል አንባቢዎችን አስፈላጊነት በተመለከተ ከገለፁት ሀሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡

ተማሪዎቹ ስላላቸው አጠቃላይ የማንበብ ፍላጎት በተደረገ የጽሑፍ መጠይቅ አብዛኛዎቹ ጥሩ የማንበብ ፍላጎት እንዳላቸው ውጤቱ ያሳያል፡፡ ውጤቱም በምዕራፍ ሁለት በተ.ቁ 2.3.1 እንደተብራራው Conley (1992) ለማንበብ አዎንታዊ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ፍላጎታቸውን በመጠቀም የተለያዩ ጽሑፎችን እያነበቡ ልምዳቸውን ማጎልበት ይችላሉ በማለት ከገለጹት ሐሳብ ጋር ይስማማል፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የገለጹትን ጥሩ የንባብ ፍላጎታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ ጽሑፎችን እያነበቡ ፈተና እንዲሰሩ በማድረግ የተገኘው ውጤት የንባብ ልምድ ፍላጎታቸው ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እገዛ እንዳላደረገ ከውጤታቸው መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የጽሑፉን መልዕክት የመገምገም ባህሪ እንደማይታይባቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም የጥናቱ ውጤት በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት በተራ ቁጥር በ2.4.1 እንደተገለጸው Million(1991) ብቁ አንባቢዎች አንዱን ጽሑፍ ሲያነቡ እንደአስፈላጊነቱ መልእክትን ለመገምገም ችሎታ አላቸው በማለት ከገለጹት ሐሳብ ጋር ይቃረናል፡፡ እንዲሁም አብዛኛዎቹ

ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ ሲያነቡ መልእክቱ ካልገባቸው ልዩ ልዩ ስልቶች /ለምሳሌ ቀድሞ በመጣ ቃል በመታገዝ ቃላትን መተርጎም፣ በቅርብ ያለፉትን አረፍተነገር ተመልሶ በድጋሚ በማንበብና ተዛማጅ ጽሑፎች በማንበብ ወዘተ/ የመሳሰሉ እየመረጡ የማንበብ ባህሪ እንደሌላቸው የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡ ይህም ውጤት በምዕራፍ ሁለት በተ.ቁ 2.5 እንደተብራራው Conly (1992) ብዙ አንባቢያን ስልቶችን እየመረጡ በመጠቀም የሚያነቡትን ጽሑፍ መልእክት ለመረዳት ይሞክራሉ በማለት ከገለፁት ሀሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሚያነቡት ጽሑፍ ልዩ ልዩ ጉድለቶች ያሉበት ከሆነ በተቻለ መጠን አስተካክለው የማንበብ ባህሪ እንደሚታይባቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህ የጥናቱ ውጤትም በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት በተራ ቁጥር በ2.5.1 እንደተገለጸው May (1990) ብቁ የሚባሉት የተለያዩ ስልቶች መጠቀም በሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ጉድለቶችን አርመው መልእክቱን ለመጨበጥ የሚጥሩ ናቸው በማለት ካቀረቡት ሃሳብ ጋር ይስማማል፡፡

ብቁ ያልሆኑ አንባብያን ባህሪያት ተብለው የሚጠቀሱ ጽሑፍን ቃል በቃል ለመሸምደድ መሞከር፣ እያንዳንዱ ቃልና ሀረግ እየለያዩ ማንበብና በአንድ እይታ አንድ ነጠላ ቃልን ብቻ እየቃኙ የማንበብ ባህሪያት በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ላይ እንደሚታይ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

ከቤተ መጻሕፍት ጋር ያላቸውን ቁርኝት አስመልክቶ ከክፍል 2 የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ብዙዎቹ ተማሪዎች ከቤተመጻሕፍት ያላቸው ትስስር ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህም በምዕራፍ ሁለት በተ.ቁ 2.1 እንደተብራራው አለም (2001) አንድ ነገር በተደጋጋሚ በተፈጸመ ቁጥር ልምድ ሆኖ የመቅረት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ የንባብ ልምድም በእንዲሁ አይነት መንገድ የሚዳብር ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ጀንበር የምናካብተው ልምድ ተደርጎ ሊታይ አይገባም፡፡ የንባብ ልምድ ይዳብር ዘንድ ሰዎችን ከህጻንነት ጊዜያቸው ጀምሮ ከመጻሕፍት ጋር ማገናኘት መሠረት መጣልን ይጠይቃል በማለት ከገለጹት ሐሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት እንዲኖራቸው የሚረዳ አንዱ መንገድ ከፍላጎታቸው ጋር አብሮ የሚሄድ መጻሕፍት ማግኘት ሲሆን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች መጻሕፍት የማግኘት እድላቸው ዝቅተኛ መሆኑን ተገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የእረፍት ጊዜያቸውን ከማንበብ ይልቅ የተለያዩ ስራዎችን መስራት እንደሚወዱ ውጤታቸው አሳይቷል፡፡

ይህም አለም (2001) ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት እንዲኖቸው ብሎም የማንበብ ልምድ ማዳበር እንዲችሉ ከአቅማቸው፣ ከደረጃቸውና ከፍላጎታቸው ጋር አብሮ የሚሄደውን መጻሕፍት ለይተን ልንጠቀማቸው ይገባል ብለው ከገለጹት ሃሳብ ይቃረናል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ አብዛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ የንባብ ልምዳቸውን ለማጎለበት የሚረዱ ሁኔታዎች የተመቻቸላቸው አለመሆኑን ውጤቱ ያሳያል ነገር ግን፣ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጥሩ የንባብ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ሆኖም ያላቸውን ጥሩ የንባብ ፍላጎት፣ ባህሪና በዚህ ፍላጎታቸው ያጎለበቱትን ችሎታ በተግባር ላይ የማዋል ብቃታቸው በዚህ ጥናት ተፈትሾ ውጤቱ ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ ዝቅተኛ ያሰኘውም ተማሪዎች ያላቸውን የንባብ ልምድና እውቀት በተግባር የማዋል ብቃታቸውን በመፈተሽ በቀረበው ፈተና አብዛኛዎቹ ያገኙተው ውጤት ከ60% በታች ስለሆነ ነው፡፡ ይህም ውጤት በምዕራፍ ሁለት በተ.ቁ 2.8 እንደተብራራው (Nuttal 1987 and Kaval 1979) ባወጡት የንባብ ቆጠራ ስልት መስፈርት ተማሪዎቹ ያላቸው የንባብ ልምድና ችሎታ በተግባር የማዋል ብቃታቸው አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለዚህም አነስተኛ ብቃት ምክንያት ያላቸው የንባብ ልምድና ችሎታ በተግባር ላይ እንዲያውሉ የሚያደርጉ ልምምዶችን አለማድረጋቸው ሊሆን ይችላል፡፡

በመጨረሻም በተማሪዎች አጠቃላይ የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ በመረዳት ችሎታ መካከል ግንኙነት እንዳለ በዚህ ጥናት ተፈትሿል፡፡ ሁለቱም ግንኙነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በተሰራው የተዛምዶ ስሌት ውጤትም (r) ከትልቅ አዎንታዊ አሃዝ በመገኘቱ በንባብ ልምድና በአማርኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩን አመልክቷል፡፡ ይህም ውጤት አዎንታዊ የንባብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት ውጤት ያስመዘግባሉ የሚል አንድምታ ያለው ይመስላል፡፡ ውጤቱም በምዕራፍ አንድ በተ.ቁ 1.1

እንደተብራራው Gerahum (1987:78) "ጥሩ የንባብ ልምድ ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ትምህርቱን ለመቀጠል መሰረታዊ ንግር መሆኑ አጠያያቂነት የለውም" በማለት የንባብ ልምድንና የትምህርት ውጤት ዝምድና ለማስገንዘብ ከሰጠው ሃሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡ እንዲሁም በምዕራፍ አንድ በተ.ቁ 1.1 እንደገለጹት Conley (1992) የተማሪዎች የንባብ ልምድ ጥሩ መሆንና አለመሆን ከጊዜ ወደጊዜ በትምህርት ውጤታቸው ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል በማለት በንባብ ልምድና በትምህርት ውጤት መካከል ዝምድና መኖሩን ለመግለጽ ከቀረበው ሃሳብ ጋር ይስማማል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

1. የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ የንባብ ልምድ ለአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተዛምዶ ለመፈተሽ ነበር።

ጥናቱ የተካሄደው በ2003 ዓመተ ምህረት በውቅሮ፣ በነጋሽና በአጉላዕ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ከሚማሩ 1880 ተማሪዎች ውስጥ 94 ተማሪዎች በተራ የእጣ ናሙና አመራረጥ ስልት ለተጠኝነት በመምረጥ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ የጽሁፍ መጠይቅና የጽሁፍ ፈተና በስራ ላይ የዋሉ ሲሆን ከተጠኚዎች የተገኘው መረጃ የተተነተነውም የዓይነታዊ የምርምር ዘዴ አካል የሆነውን የገላጭ ዘዴ በመጠቀም ነው።

በተጨማሪም ከተጠኚዎች የተገኘውን ውጤት ለመተንተንም መቶኛ፣ አማካይ ውጤት፣ መደበኛ ልዩነት፣ የተዛምዶ ስሌት እና t-test በተግባር ላይ ውለዋል። በዚህም መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል።

### 5.1 ማጠቃለያ

- ከጽሁፍ መጠይቅ ትንታኔ በአብዛኛው ተማሪዎች ጥሩ የንባብ ልምድ እንደሌላቸው የሚያመለክት ከ63% በታች ውጤት ተገኝቷል። ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በመምህራን የተፈጠሩላቸውን ጥሩ አጋጣሚዎች በመጠቀም ጥሩ የንባብ ልምድ ማጎልበት እንዳልቻሉ ውጤት ያሳያል። ስለዚህ በመምህራን የተደረገው እገዛ በቂ አለመሆኑን ከውጤት መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የብዙዎቹ ተማሪዎች የንባብ ልምድ የሚያመረቃ አይደለም።
- በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ጥሩ የንባብ ፍላጎት እንዳላቸው የጽሑፍ መጠይቁ ውጤት አመልክቶዋል። ነገር ግን ይህን ፍላጎታቸውን በተግባር ለማዋል እንዳልቻሉ ከፈተናው ውጤት መረዳት ተችሏል። ከዚህም ሌላ በርካታ ተማሪዎች የብቁ አንባብያን ባህሪያት እንደማይታይባቸው ውጤቱ ያሳያል።

- አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በተፈጠሩላቸው ውስን ምቹ ሁኔታዎች ጥሩ የማንበብ ፍላጎት ቢኖራቸውም ከትምህርት ቤት ውጭ ተገቢ እገዛ ስላልተደረገላቸው የንባብ ልምድ እንዳላካበቱ ታይቷል፡፡ በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት መካከል ያለው የተዛምዶ ስሌትም ተሰልቶ ትልቅ አዎንታዊ ኣሃዝ (0.66) ተገኝተዋል፡፡ ከዚህም ከጥናቱ ውጤት በመነሳት በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት የአንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ዝምድና አዎንታዊ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህም አዎንታዊ የንባብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች የተሻለ የአማርኛ ውጤት ያስመዘግባሉ የሚል አንድምታ ያለው ቢመስልም የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤታቸው ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል ያሳየናል፡፡

- በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ውጭ ለንባብ ልምድ ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ መጻሕፍት ማግኘት እንዳልቻሉና የወላጆች እገዛም አናሳ መሆን ውጤቱ ይጠቁማል፡፡ እንዲሁም ከቤተ መጻሕፍት ያላቸው ቁርኝት የላላ መሆኑን ውጤቱ ያመለክታል፡፡

በተማሪዎች የንብብ ልምድ ላይ ተጽዕኖ የሚያስችሉ ነገሮች እንዳሉ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ከፍ ለማድረግ የተለያዩ አከላት እንዳሉም ተጠቅሷል፡፡ ከነዚህ መከከል፡-

- ተማሪዎቹ ሚኖሩበት አከባቢ
- የተማሪዎቹ ውስጣዊ ስሜት
- የተማሪዎቹ ማህበራዊ ፍላጎት
- የተማሪዎቹ ስነ-ልቦናዊ ዝንባሌ

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከዚህ አንጻር የተማሪዎች የንብብ ልምዳቸውም ሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ተማሪዎቹ የንብብ ልምዳቸውና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች አከኝነት መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ እነሰም፡-

- በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ ለንብብ ልምድ ጠቃሚ የሆኑ መጻሕፍትን ማግኘት አለመቻላቸው፡-

- ወላጆች የልጆቻቸውን የንብብ ፍልጎት ከማሟላት አንጻር ዝቅተኛ በመሆኑ፤
- መምህራን በየጊዜው በተለያዩ የንብብ ልምድን የሚያዳብሩ ተግባራዊ ልምምዶችንና መከራዎችን ለተማሪዎች ባለማቅረባቸው፤
- መምህራን የንብብ ልምድን ሊያዳብሩ የሚችሉ ልዩልዩ መጻሕፍትን እንዲያነቡ በመጠቆም የላቀ እገዛ አለማድረጋቸው፤
- ተማሪዎች ከቤተ-መጻሕፍት ገብተው የንብብ ልምዳቸውን የሚያዳብሩበት ጊዜ አናሳ በመሆኑ እና
- የተማሪዎች የንብብ ስልት ያልዳበረበመሆኑ የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና የመሳሰሉት በአንድነት የተማሪዎች የንብብ ልምድ ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት የሆኑ ናቸው፡፡ የተማሪዎች የንብብ ልምድ ዝቅተኛ ከመሆኑ በላይ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረዋል፡፡

## 5.2 መፍትሔ ሐሳብ

ይህ ጥናት በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተነሳው መሰረት ውጤቱ እንደሚያመለክተው የንባብ ልምድና የአንብቦ መረዳት ችሎታ አዎንታዊ ግንኙነት አለው፡፡ ማለትም የንባብ ልምዳቸው ዝቅተኛ ስለሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ፡-

- ✓ መምህራን በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎችን የንባብ መርሃግብርና ሌሎች የንባብ ልምድ የሚጎለብቱባቸውን ስልቶች በማመቻቸት የተማሪዎቹ የንባብ ልምድ እንዲጎለብት ቢያደርጉ፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በትምህርት ቤት ውስጥና በየቀበሌው የተጠናከሩና የተደራጁ መጻሕፍት ቤቶች የሚቋቋሙበትና ያሉትም የሚጠናከሩበት መንገድ ቢፈለግ፣
- ✓ የትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር በገበያ ላይ የሚገኙትን መጻሕፍት ገዝተው በመጻሕፍት ቤት ተማሪዎች በቀላሉ የሚያገኙበት መንገድ ቢያመቻቹ
- ✓ ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ መጻሕፍትን እያነበቡ የንባብ ልምዳቸውን ቢያጎለብቱ፤

- ✓ ሌላው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ መጻሕፍት እንደማይጠቀሙ ከዚህ ጥናት ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች የንባብ ልምድ ይበልጥ እንዲዳብር ትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች ቤተ መጻሕፍትን የሚጠቀሙበት መንገድ ቢያመቻቹ ጥሩ ነው፡፡ እንዲሁም መምህራን ተማሪዎቹ ቤተመጻሕፍትን እንዲጠቀሙ ግፊት ቢያደርጉ፤

- ✓ መምህራን ተማሪዎቹ ያላቸውን የማንበብ ልምድ በተግባር ላይ ለማዋል ብቃታቸውን ለማሻሻል እንዲችሉ በየጊዜው የተለያዩ ተግበራዊ ልምምዶችንና ሙከራዎችን ለተማሪዎች በማቅረብና አስፈላጊ የሆኑ መጻሕፍትን በመጠቀም የላቀ እገዛ ቢያደርጉላቸው፤

- ✓ በመጨረሻም በዚህ ጥናት ተማሪዎች የንባብ ፍላጎታቸው በአብዛኛው ጥሩ መሆኑ ቢረጋገጥም የዳበረ የንባብ ልምድ ስለሌላቸው የንባብ ልምድና ችሎታን በተግባር የማዋል ብቃታቸው ሲፈተሽ ዝቅተኛ መሆኑ ታይቷል፡፡ ስለዚህ ልምድ በድግግሞሽ የሚዳብር ነው፡፡ አንድ ነገር በተደጋጋሚ በተፈጸመ ቁጥር ልምድ ሆኖ የመቅረት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ የንባብ ልምምድም በእንዲህ አይነት መንገድ የሚዳብር ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ጊዜ የምናካብተው ልምድ ተደርጎ ሊታይ አይገባም፡፡ ስለዚህ የንባብ ልምድ ይዳብር ዘንድ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በየጊዜው ከመጻሕፍት ጋር ማገናኘትና ወደ ቤተ መጻሕፍት የሚሄዱበትን መንገድ መሰረት መጣልን ይጠይቃል፡፡ ይህንን መሰረት የመጣል ኃላፊነት ደግሞ ትምህርት ቤቶች ብቻ የሚሸከሙት አይደሉም፡፡ ወላጆችም ከትምህርት ቤቶች የማይተናነስ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ፍላጎት ወደ ተግባር ለመለወጥ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ሙሉ ተሳትፎና በቂ ልምምድ ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡

## ዋቢ መፅሃፎች

ማስተዋል ውብቱ(1989):: "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች *በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ::"* የማስተርስ ማሚያ ጥናታዊ ጽሁፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ:: (ያልታተመ)

ማረው አለሙ(1987):: "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ስነጽሑፍ ክፍል በ2ኛ አመት ተማሪዎችበግልና በቡድን የሚጻፉ ድርሰቶች ንጽጽራዊ ጥናት::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ:: (ያልታተመ)

ሰለሞን ሀለፎም (1989):: "አማርኛን በማስተማሪያ ዘዴነት የቃል ጽሕፈት ሚና::"ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: (ያልታተመ)

በድሉ ዋቅጅራ (1988):: «ተሳታፊነት-ጭምትነት የስብዕና ዓይነት ከድርሰት መጻፍና ከአምብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፤ በሶስት ኮሌጆች ተማሪዎች ላይ ያለ የተደረገ ጥናት::" ለማስተርስ ማሚያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: (ያልታተመ)::

ባየ ይማም (2002):: *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋሰው::* አልፋ አሳታሚ ድርጅት::

ብርቱኳን እሸቱ (1993):: "የንባብ ልምድ ከፅህፈት ክሂል ጋር ያለው ዝምድና ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::(ያልታተመ)

ተስፋዬ ሸዋዬ (1986):: *አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር::* አዲስ አበባ:: ት.መ.ማ.ማ.ድ

ተፈራ በጋሻው (1998):: "ለዘጠነኛ ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ:: (ያልታተመ)

ጌታቸው አዱኛ (1986):: "ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦችየብቃት ደረጃ::" ለማስተርስ ማሚያ የቀረበ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ: :(ያልታተመ)

ግርማ አውግቸው (1988)። "በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል በበሳል ድርሰት እና በሌሎች ኮርሶች ተማሪዎች በአማርኛ የሚከውኗቸው የጽሕፈት ሥራዎች ንጽጽራዊ ጥናት።" ለማስተርስ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ። (ያልታተመ)

አለማየሁ ጸጋዬ (1986)። "በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጽሙት ስህተቶች ዋና ዋና ምንጮች።" ለማስተርስ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ። (ያልታተመ)

አለም እሸቱ (2001)። *"የወጣቶች የንባብ ልምድ ፍተሻ በአዲስ አበባ ወጣቶች መነሻነት።"* መድብለ ጉባኤ 61-69።

የኔሰው ደሴ (1990)። "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸው ያፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋፅኦ።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

Arcy.P.D (1973). *Reading for meaning*. Landon፡ Hotchinson Edu Ltd.

Badraw (1992) "The Reading Dilemma; Meeting Individual Needs." *English Teaching Forum.* 30/3:16-19

Bastidas, AJ (1946). Clear procedure as Teaching Technique to Improve Reading Comprehensive. Cambridge: Cambridge University Press.

Carbo, M. (1991). *Teaching students to read through their individual learning style.* Boston Allyn and Bacon

Carrel,L.P and Define, J. (1995). *Interaction Approach to 2nd language reading*. New York: Cambridge University Press.

Charles A.P. (1983). Reading Ability. New York: Oxford University Pries.

Chubby, C. (1991). "Individualizing your reading program for advanced beginning levels" *English teaching forum*. 30/3: 50-51.

Conley M.W. (1992). *Contents Reading Instruction፡ A communication Approach.* New York: CUP.

Farrant, I.S 1 (1977). *Principle and Practice of Education*. (2nd ed) Cambridge: CUP London Long Man Group. LteV.

Fry, E. (1963) *Reading fastens.* Cambridge; Cambridge University press

Graham. RT. (1967). "Content reading and the recreation meaning" in *ELT Journal,* 76/2:98- 99.

Greenall, S and Swant, M. (1996). *Effective Reading* (8th ed). Cambridge; Cambridge university press.

Greenwood,J. 1981 " Comprehension and Reading." *In the teaching of English as an international Language*: pp 81-110.

Grellet, F (1995). *Developing Reading skills.* Cambridge: Cambridge University Press.

Gray,W.S and Stoiger.R (1969). The Teaching of Reading and Writing(2nd ed.) Switzewrland. UNESCO.

Heaton,J.B. (1975). *Writing English Language Tests: A practical Guide far teachers of English as a second language of foreign Language.* London: Longman.

Huyland, K. (1990). "Purpose and Strategy: Testing extensive Reading skills" *English Teaching Forum* 38/2:14-17.

Kavale, K. (1979). "Selecting and Evaluating Reading tests". *In R. Shreier (ed). Reading Test and Teachers:* Practical guide. Pp. 9-32.

Key, C.N. (1979). *Practical Teaching*. London: Event Brothers, Ltd.

May, BF. (1990) . *Reading as Communication an interactive approach.* (3rd ed) New York Macmillan Publisher Company.

Millan, D. (1991).*Developing Reading skills*. New York: Cup.

Naroyanaswamy, K.R. (1975). "The measurement of reading ability" *Journal of English Language Teaching* 29/2: pp 143-150.

Nelson, G.L (1984). "Reading: A student Centered Approach," English *Teaching Forum,* 2214.2-4.

Niles, Olives. (1972) "Reading skills common to the content Areus." In Melnik, Amelian and Jhon inerritt. (ed). *The reading curriculum.* Aylesbury: the Open University Press. Pp:27 40.

Nuttall, C. (1982) *Teaching Reading Skills in a foreign Language* London: Heineman Educational Books.

Omaggio, Alice (1983) "Methodology in Transition: The new focus on proficiency." *The modern Language Journal.* 67/4 pp 330-341.

Sil berstein, S. (1994). Techniques and resources in Teaching Reading Oxford University Press.

Smith F. (1973) *Psycholinguists and Reading* New York: Rinehart and Winston

Smith, E (1997). *How Children Learn to Read.* London: Addison Wesley Longman New Zeland Limited.

Thorinike, R.M (1997*) Measurement and Evaluation in Psychology and Education* (6th ed). Upper Sonddle River: Merrill Imprint of Prentile Hill .

# አበሪዎች

አባሪ:1

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## በተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማወቅ የሚረዳ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡በመሆኑም አንተ/ቺ/ የምትሰጠው/ጪው/ ለጥናቱ ዓላማ ስኬት ትልቅ ሚና ስላለው ጥያቄችን በመመለስ እንድትተባበሩኝ በትህትና እየጠየቅሁ ይህን መጠይቅ በመሙላትህ/ሽ/ ስለተባበርከኝ/ሽኝ በቅድሚያ ከፍ ያለ ምስጋና ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

### አጠቃላይ መረጃ

**መመሪያ 1፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መረጃ ስጥ/ስጪ/**

1. የክፍል ደረጃህ/ሽ/
2. ፆታ ወንድ-------------ሴት-----------
3. እድሜ -----------------

መመሪያ 2፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች እያንዳንዱን በማንበብ በፊት ለፊት ከቀረቡት 5 አማራጮች በግልህ/ሽ/ ይበልጥ የሚስማማህን/ሽን/ አንዱን ብቻ በመምረጥ በባዶ ቦታው ላይ ይህንን (✓) ምልክት በመጠቀም አመልክት/ቺ/ ::

| ተ/ቁ | ዝርዝር ነጥቦች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም | መወሰን አልችልም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከምንም ነገር በላይ መጽሐፍን ማንበብ እወዳለሁ | | | | | |
| 2 | አልፎ አልፎ መጽሐፍን በመግዛት አነባለሁ | | | | | |
| 3 | መኖሪያ ቤት ውስጥ በርካታ መጻሕፍት ስላሉ አነባለሁ፡፡ | | | | | |
| 4 | መጻሕፍትን ከማንበብ ይልቅ ሌላ ስራ መስራትን እመርጣለሁ | | | | | |
| 5 | መጻሕፍትን ለማንበብ ከቤተ መጻሕፍትን ተውሼ አላውቅም | | | | | |
| 6 | መጻሕፍትን እንዳነብ ካልታዘዝኩ በስተቀር የማነበው አልፎ አልፎ ነው | | | | | |
| 7 | ሰዎች በነገሩኝ አንድ ሐሳብ ላይ ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት መጻሕፍትን አላነብም | | | | | |
| 8 | ቤተ መጻሕፍት ውስጥ አዘውትሬ በመግባት አነባለሁ | | | | | |
| 9 | መምህራን በክፍል ውስጥ ምንባብ ሲያስነብቡን እንዴት ማንበብ እንዳለብኝ ያስረዱኛል | | | | | |
| 10 | መምህራን በክፍል ውስጥ በአብዛኛው በግል የለሆሳስ ንባብ ስልት ያስነብቡኛል | | | | | |
| 11 | መምህራን የተለያዩ ለንባብ የሚሆኑ መጻሕፍትን እየጠቆሙኝ አነባለሁ | | | | | |
| 12 | የማንበብ ፍላጎት ያሳደሩብኝ የማደንቃቸው አንባቢዎች በአካባቢዬ አጋጥመውኛል | | | | | |
| 13 | ቤተሰቦቼ የማነባቸው መጻሕፍት ገዝተውም ሆነ ተውሰው ይሰጡኛል | | | | | |
| 14 | አንድ ጽሑፍ ሳነብ መልእክቱን ለመገምገም ጥረት አደርጋለሁ | | | | | |
| 15 | አንድን መጽሐፍ ሳነብ መልእክቱ ካልገባኝ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ለመረዳት እሞክራለሁ | | | | | |
| 16 | በማነበው ጽሑፍ ውስጥ የተለያዩ ስህተቶች ሲያጋጥሙ በማስተካከል አነባለሁ፡፡ | | | | | |
| 17 | አንድ ጽሑፍ ሳነብ ከጸሐፊው ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቼ የመወያየት ስሜት ይሰማኛል | | | | | |
| 18 | በማነብበት ጊዜ በእያንዳንዱ እይታዬ የአንድ ነጠላ ቃልን በመቃኘት አነባለሁ | | | | | |
| 19 | በማነብበት ጊዜ በጣቴ ወይም በሹል ነገር መጠቆም እወዳለሁ | | | | | |
| 20 | አንድን ጽሑፍ ሳነብ መልእክቱ ካልገባኝ ጽሑፉን ቃል በቃል ለመሸምደድ እሞክራለሁ | | | | | |

ከክፍል ሁለት የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

የማንበብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች ከቤተ መጻሕፍት ጋር ያላቸውን ቁርኝት አስመለክቶ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1. | "ወደ ቤተ መጻሕፍት ምን ያህል ጊዜ ትሄዳለህ/ሽ"? | | |
| | ሀ. በየቀኑ | 15 | 15.9 |
| | ለ. በየሳምንቱ | 11 | 11.7 |
| | ሐ. በየወሩ | 58 | 61.7 |
| | መ. ሄጄ አላውቅም | 10 | 10.6 |
| 2. | የምታነቧቸውን መጻሕፍት የምታገኙዋቸው በምን ዓይነት መንገድ ነው? | | |
| | ሀ. በግዢ | 14 | 14.89 |
| | ለ. ከቤተ መጻሕፍት በመዋስ | 7 | 7.4 |
| | ሐ. ከዘመድ ወዳጅ | 60 | 63.8 |
| | መ. አላነብም | 12 | 12.7 |
| 3 | በአንተ/አንቺ ግምት የንባብ ልምድህ/ሽ ምን ያህል ነው? | | |
| | ሀ. ከፍተኛ | 18 | 19.14 |
| | ለ. መካከለኛ | 52 | 55.3 |
| | ሐ. ዝቅተኛ | 24 | 25.5 |

ከጽሑፍ መጠይቅ (ክፍት ጥያቄዎች የተገኘ መረጃ)

ማንበብ ፍላጎታቸውን ለማወቅ ተብሎ የቀረበው ጥያቄ ተ.ቁ 1መጽሐፍ ማንበብ ትወዳለህ/ሽ? አይደለም ከሆነ መልሳችሁ ለምን? ለሚለው ጥያቄ እና ጥያቄ ተ.ቁ 2 የእረፍት ጊዜህን/ሽን የምታሳልፈው/ፊው በምን መልኩ ነው? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፡-

❖ መጻሕፍት ከማንበብ ይልቅ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚቀርቡ መዝናኛዎችን መመልከት፣ ሙዚቃ ማዳመጥ፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ እንደሚወዱና ጊዜያቸውን በዚሁ መልኩ እንደሚያሳልፉ ገልጸዋል፡፡

በተራ ቁ.3 በትምህርት ቤትህ/ሽ ወይም በቤትህ/ሽ ንባብን እንዳትለማመድ/ጂ የሚያደርግህ/ሽ ነገር ግለጽ/ጪ ለሚለው ሃሳብ የሰጡት ምላሽ፡-

❖ አንብቦ ለመረዳት ችግር ስላለብኝ ሳነብ አይገባኝም፣ በጊዜ ማጣት የተነሳ ማንበብ አልችልም፣ ሴት ልጅ በቤት ስራ ወላጆቿን ማገዝ እንጂ ማንበብ አይፈቀድላትም የሚሉትን ምላሽ ሰጥተዋል።

በተራ ቁ.4 አስተማሪህ/ሽ በክፍል ውስጥ ለንባብ ልምድ የሚያደርግልህ/ሽ እገዛ ተገቢ ነው ትላለህ/ትያለሽ? አዎ ከሆነ መልስህ/ሽ እንዴት? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ

❖ አስተማሪዬ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ከፋፍለው ያስነብቡኛል፣ በማለት መልስ ሰጥተዋል።

በተራ ቁ.5 በአንድ ርዕስ ላይ መረጃ ሰብስበህ/ሽ አጭር ጽሑፍ እንድታቀርብ/ቢ ብትታዘዝ/ዢ መረጃ ከየት ታገኛለህ/ሽ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽም

❖ ብዙዎቹ ተማሪዎች ሰው እጠይቃለሁ የሚል መልስ ሲሰጡ  አናሳው ደግሞ ከቤተ መጻሕፍት አስፈላጊውን መጽሐፍ  እፈልጋለሁ ሲሉ መልስ ሰጥተዋል። ከዚህ የምንረዳው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም ልምድ አለመኖራቸው  የሰጡት ምላሽ አመላካች ነው።

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል
# የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

## በተማሪዎች የሚሰራ ፈተና

የዚህ ሙከራ ዓላማ ተማሪዎች ስለንባብ ልምድ ያላቸውን ግንዛቤ ለመረዳት ብሎም የንባብ ችሎታቸውንና እውቀታቸውን እንዴት በተግባር እንደሚያውሉት ለመገምገም ነው ። ከግምገማው የሚገኘው ውጤት ተማሪዎች ካላቸው የንባብ ልምድ ጋር ተገናዝቦ በተማሪዎች የንባብ ልምድና በአማርኛ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ዝምድና ለማጥናት አጋዥ መረጃ ይሰጣል ።

ሙከራውም ሶስት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎች ስላላቸው ጠቅላላ እውቀት መረጃ ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በተማሪዎችና በምንባቡ መካከል ያለውን መስተጋብር ለመገምገም ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሶስተኛው ክፍል ደግሞ በተማሪዎችና በተሰጡት አውዶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመፈተሸ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ክፍል ቅደም ተከተሉን መሰረት አድርጎ ይሰራል፡፡

መመሪያ አንድ ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መረጃ ጻፍ/ፊ፡፡

1. የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ

1.የክፍል ደረጃህ/ሽ/

2.ፆታ ወንድ--------------ሴት------------

3. እድሜ -------------------

መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ ቀጥሎ በወቅትና ስነ ቃል ዙሪያ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ስለዚህ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ተገቢ ናቸው ብለህ/ሽ/

የምታስባቸው/ቢያቸው/ መልሶች በተሰጠው ባዶ ቦታ ፃፍ/ፃፊ

1. ሥነ-ቃል ምንድነው?

_______________

2. የሥነ-ቃል ፈጣሪ ወይም ባለቤት ማነው? ትላለህ/ትያለሽ

_______________

3. የሥነ-ቃል ዘርፎች ምን ምን ናቸው?

_______________

4. ወቅትና ሥነ-ቃል እንዴት ሊዛመዱ እንደሚችሉ ግለፅ/ግለጪ

_______________

5. የምንባቡ ዋና ሐሳብ ምንድነው?

_______________

II ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ካነበብክ/ሽ/ በኋላ ለጥያቄው ተገቢውን መልስ ከቀረቡት

አማራጮች መልስ/ሽ/

1. በገበሬ ሕይወት ውስጥ ወቅትና ስነቃል "ድርና ማግ" ናቸው በሚል ውስጥ ድርና ማግ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ተከታታይነት ያላቸው ለ. የማይገናኙ ሐ. የማይስማሙ መ. የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው

2. ለሞኝ ሰኔ በጋው፣መስከረም ክረምቱ የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ምንን ይገልፃል?

ሀ. ብርታትን ለ. ስልቹነትን ሐ. ማረስን መ. ረዳት መሆንን

3. "በሚያዝያ ጎመን የዘራ ክረምቱን ሁሉ በላ" የተባለበት ምክንያት ምንድነው?

ሀ. ጎመን አዝመራ መምጣቱን አመላካች ስለሆነ ነው

ለ. ጎመን የክረምት አዝመራ እስኪደርስ ማቆያ ምግብ ስለሆነ ነው

ሐ. ከቂጣ የበለጠ ጎመን ስለሆነ ነው

መ. ጎመን የሚዘራው በሚያዝያ ስለሆነ ነው፡፡

4. አዝመራን በማህበር የመሰብሰብ ልምድ ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. ሞራል ለ. አጨዳ ሐ. ደቦ መ. ማረስ

5. "በጥቅምት አንድ አጥንት የሚባለው ለምንድነው?

ሀ. የጥቅምት አየር ሁኔታ ቀዝቃዛ መሆኑን ለማመላከት

ለ. የጥቅምት ዝናብ አነስተኛ መሆኑን ለማመላከት

ሐ. ጥቅምት የጥጋብ ወቅት መሆኑን ለማመላከት

መ. ጥቅምት ጎመን የሚጠፋበት መሆኑን ለማመላከት

## ምንባብ አንድ

### ወቅትና ስነ-ቃል

በገበሬ ሕይወት ውስጥ ወቅትና ስነቃል ድርናማግ ናቸው። ስለዚህም ገበሬ ወቅትን ተከተለ ተግባራቱን ሲያከናውን በስነ ቃል አማካይነት ማዜሙና መንጎራጎሩ የተለመደ ነው።

በሰኔ ደመናው ሲያስገመግም፣ ዝናቡ ሲያናፋ ገበሬው ሞፈር፣ቀንበርናጅራፍ የመሣሠሉትን የእርሻ መሣሪያዎች ከየተሰቀሉበት አውርዶ በቡሬ፣በመጋል፣በሶረን ወዘተ በሚባሉ በሬዎች እርሻውን ያጧጡፈዋል። በረደኝ፣ ራበኝ፣ ዝናብ መታኝ ሳይል ከነቤተሰቦቹ ልብሱን ባጭር ታጥቆ ያርሳል፤ ይጎለጉላል፣ ይዘራል። ይህን ጊዜ ታዲያ በሬዎቹም ሆነ ቤተሰቦቹ ድካም እንዳይሰማቸው እንዲህ እያለ ያነቃቃቸዋል።

ሰኔና ሐምሌ፣ ግምግም ሲል፣
የቀኙ በሬ፣ አውጣኝ አውጣኝ ሲል፣
የግራው በሬ አውጣኝ አውጣኝ ሲል፣
የእርፉ ልማም፣ ጎጆ ሲመስል
አርፎ ይወድቃል ከማነቀው ስር።
ጎበዝ ልንገራችሁ ጎበዝ እርሻ እረሱ
ካልሆነም መንኩሱ እየወለዳችሁ ልጅ አታስለቅሱ።

ለሞኝ ሰኔ በጋው፣ መስከረም ክረምቱ እንዳይሆን እንዲህ እንዲህ እያለ እሱ በርትቶ አጋሮቹን ያበረታታል።
በሐምሌና ነሐሴ ገበሬ የምግብ ዓይነት አያማርጥም። ሚያዚያ ጎመን የዘራ፣ ክረምቱን ሁሉ በላ ይባላልና አዝመራው እስኪደርስለት ቂጣውን፣ቆሎውን፣ ጎመኑን ወዘተ እየበላ ይጠብቃል። ወደ ነሐሴ አጋማሽ ላይ የገበሬው ልጆች አዝመራቸውን ከወፍ እየጠበቁ ጅራፋቸውን ያጮሐሉ። ወዲህ ማዶና ወዲያ ማዶ ሆነውም፡-

አህያ መጣች ተጭና ወይራ
ችግር ሲያልፍ ነው፣ደረሰ አዝመራ።
አህያ መታች ተጭና አብሽ
መስከረም ጠባ ብላ ጥንቅሽ ይባላሉ።

ክረምት ቦታውን ለመኸር ሲለቅ ዝናቡ ያበራል፣ ሰማዩም ይጠራል። መኸር የአዝመራ መሰብሰቢያ ጊዜ ነው። ከጥቅምት ወር ጀምሮም አዝመራ የተለመደ ነው። ጥቅምት ደግሞ ቅዝቃዜ የሚበረታ ነው። በጥቅምት አንድ አጥንት ፣ ውሃስ የጥቅምት ነበር የሚጠጣው በነበር የሚሉት ምሳሌያዊ ንግግሮችም የሚገልጹት ይህንኑ የአየር ሁኔታ ነው።
ገበሬ ሰብሉን በማህበር የመሰብሰብ ልምምድ አለው። ይህ የማህበር ስራ ደቦ ይባላል። ለደቦ የተጠሩ ገበሬዎች ሞራል የሚያነሳሳ ዜማ እየሰማ አጨዳውን ይያያዙታል፣ እንዲህ እያሉ፡-

የወይና ጌታ፣ የሻሾ በራ፣
አንድ ሁዳድ መሬት ጠምዶ እሚዘራ።

አጫጅ አጫጁን እኛ ስናውቀው፣
ማጭድ በቅፌን ማን ደባለው።
እንረስ ካላችሁ ተማክረን እንረስ
መሬት ዳዋ እንዳይለብስ እህል እንዲታፈስ።

ገበሬ አዝመራውን ወደ ጎተራ የሚያስገባው በታሕሳስ ወር ነው። በዚህ ወር ክምሩ፣በተንጣለለ አውድሜ ላይ ይዘረጠጥና ይወቃል። ለስራ የመጣው ደቦኛም መንሹን፣ ለዳው፣ መጥረጊያውን ወዘተ ያገዘ አውድማውን በመክበብ እንዲህ እያለ እህሉን ይወቃል፣ ያበራያል።

ኧረ በሬ ደጉ ኧረበሬ ደጉ
ላንተ ያደግድጉ ለባለማዕደጉ
ሲያርሰው በድግር ሲያሸሸው በግር
የሰው የኛ ጌታ በሬው ምን ያምር
የበሬው ውለታ መጫወት ነው ማታ
በሰፊው ገበታ በዋንጫ ጋጋታ።

እንዲህ እንዲህ እያለ የተወቃው አዝመራ ጎተራ ይገባል። ገበሬም ለሌላ ተመሳሳይ ስራ ይሰናዳል።
/ከአዝመራ መጽሔት ለምንባብ የቀረበ/

መመሪያ አራት ፡- በንባብ ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

1) ኣንድ ፅሁፍ እያነበብክ /ሽ የኣንድን ኣንቀፅ ሃሳብ ኣንብበህ /ሽ እንድትረዳ /ጂ ብትታዘዝ /ዢ ምን ታደርጋለህ /ታደርጊያለሽ/ ?
2) በቂ ሰዓት ሳይሰጥህ/ሽ ያንድን ኣንቀፅ ሃሳብ ኣንብበህ/ሽ እንድትረዳ /ጂ ብትታዛዝ /ዢ ምን ታደርጋለህ /ታደርጊያለሽ/ ?
3) ኣንድን ፅሁፍ እያነበብክ /ሽ እያለ በመሃከል) ያንድን ፀሁፍ ሃሳብ ባይ ገባህ /ሽ ሃሳቡን ለመረዳት ምን ታደርጋለህ /ታደርጊያለሽ/ ?
4) በኣንድ ፅሁፍ ውስጥ ኣዲስ ቃል) ብያጋጥምህ /ሽ ሃሳቡን ለመረዳት ምን ታደርጋለህ /ታደርጊያለሽ/ ?
5) ለተወሰኑ ቀናት ከትምህረት ቀርተህ/ሽ የአንድ ምዕራፍ ትምህርት ቢያመል)ጥ/ሽ ትምህርቱን ለማካካስ ምን ስል)ት ትጠቀማለህ/ ትጠቀሚያለሽ/?

መመሪያ 2፡- በንባብ ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹ በጥሞና ካነበብክ/ሽ/ በኂላ ተገቢ መፍትሄ ነው ብለህ/ሽ/ የምታስበውን/የምታስቢውን ፃፍ/ፊ

1. አንድ ፅሁፍ እያንበብክ/ሽ/ የአንድን አንቀፅ ሃሳብ አንብበህ/ሽ እንደትረዳ/ጂ ብትታዘዝ/ዢ ምን ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ /?
2. በቂ ሰዓት ሳይጠስህ/ሽ ያንድን አንቀፅ ሃሳብ አንበብህ/ሽ እንድተረዳ /ጂ ብትታዛዝ ዢ ምን ታደርጋለህ /ታደርጊያለሽ/?
3. አንድን ፅሁፍ እያነበብክ/ሽ እያለ በመሃከል ያንድን ፁሁፍ ሃሳብ ባይ ገባህ/ሽ ሃሳቡን ለመረዳት ምን ታደርጋለህ/ተደርጊያለሽ?

4. በአንድ ፅሀፊ ውስጥ አዲስ ቃል ብያጋጥምህ/ሽ ሃሳብን ለመረዳት ምን ታደርጋለህ/ ታደርጊያለሽ?

5. ለተወሰኑ ቀናት ከትምህርት ቀርተህ/ሽ የአንድ ምዕራፍ ትምህርት ቢያመልጥ/ሽ ትምህርቱን ለማካካስ ምን ስልት ትጠቀማለህ/ትጠቀሚያለሽ/?

ከክፍት የፁሁፍ ፈተና የተገኘ መረጃ

1.አንድ ፅሁፍ እያንበብክ/ሽ/ የአንድን አንቀፅ ሃሳብ አንብበህ/ሽ እንደትረዳ/ጂ ብትታዘዝ/ዢ ምን ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ /?

- ሰው እጠይቃለሁ
- የተለያዩ መፃሐፍት አነባለሁ
- ምንባቡን እተወዋለሁ

2. በቂ ሰዓት ሳይጠስህ/ሽ ያንድን አንቀፅ ሃሳብ አንበብህ/ሽ እንድተረዳ /ጂ ብትታዛዝ ዢ ምን ታደርጋለህ /ታደርጊያለሽ/?

- ሰዓት እንዲጨመርልን እጠይቃለሁ
- በፈጥነት አነባለሁ
- እየዘለልኩ አነባለሁ

3. አንድን ፅሁፍ እያነበብክ/ሽ እያለ በመሃከል ያንድን ፁሁፍ ሃሳብ ባይ ገባህ/ሽ ሃሳቡን ለመረዳት ምን ታደርጋለህ/ተደርጊያለሽ?

- በርከታ ተማሪዎች ሰው እጠይቃለሁ ሲሉ አነሳውን ደግሞ የተለያዩ ስልቶች በመጠቀም ለመረዳት እሞክራለሁ፡፡

4. በአንድ ፅሀፊ ውስጥ አዲስ ቃል ብያጋጥምህ/ሽ ሃሳብን ለመረዳት ምን ታደርጋለህ/ ታደርጊያለሽ?

- ብዙዎቹ ተማሪዎች ሰው አጠይቃለሁ ሲሉ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ የተለያዩ መፀሐፍትን በማንበብ የቃሉን ትርጉም እፈልጋለሁ ብለዋል፡፡

5. ለተወሰኑ ቀናት ከትምህርት ቀርተህ/ሽ የአንድ ምዕራፍ ትምህርት ቢያመልጥ/ሽ ትምህርቱን ለማካካስ ምን ስልት ትጠቀማለህ/ትጠቀሚያለሽ/?

- ከክፍል ውጭ አስተማሪን እንዲያስረዳኝ እጠይቃለሁ
- ተማሪዎች የፃፉቱን ማስታወሻ አነባለሁ፣ ተማሪዎች እንዲያስረዱኝ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡

# ምንባብ ሁለት

በአንዳንድ መሰረት ሃሳቦች በጭውውት ሆነ በመድረክ ላይ መወያየት ትምህርት ለመቅሰም የሚጠቅም ከመሆኑም በላይ አእምሮን በመልካም አስተሳሰብ ያንፃል ። መልካም ውይይት ከልምድ ከተገነባ የእውቀት አድማስ ይሰፋበታል። የስራችሎታ ይዳብርበታል እውነትነት ቀና በሆነ መንገድ የሚያረካ ውይይት ሲካሄድ በተለያዩ የሃሳብ ውጣውረድ በየፊናቸው የሚሄዱ አስተያየቶች አንድ አቅጣጫ ይይዛል ።ያልተዛባና የሰለጠነ የነገሮች ኣተያይ ለማስገኘት በሳይንሳዊ አመለካከት የዳበረ ኣስተሳሰብን ግላዊ ባህሪ ለማድረግ የሚጠቅሙ ዘዴዎች አንድና ዋነኛው ነው።

ስለሆነም ውይይት ለመልካምነት የሚበቃው በኣግባቡ ሲካሄድና ስጨ ተቀባይነት መንፈስ ሲኖር ነው። ግቡን የሚመታው የኣነጋገርና የኣስተሳሰብ ጤናማ ሂደት በኣላማውና በስርኣቱ ሲጠበቅ ነው።ሀሳብስምምነት ላይ ካልተደረሰ ወይም የኣለመግባባት ችግር ካልተፈታ ክርክር ከተላል ።

ለክርክር መሄድ ኣስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል በመጀመሪያ የሚመጣው በጎ ፈቃድና ፍላጎት ነው ። በጎፈቃድና ፍላጎት የሌለው ሰው ልከራከርህ ቢሉት ቶሎ ይሰለችና ከነገር ለመግለል ለምክንያት ማስረጃ ሳይቸገር ልክ ነኝ ብሎ ድርቅ ሲል ይችላል ።

ለመልካም ውይይትና ክርክር የተሳታፊዎች በጎ ፈቃደና ፍላጎት ብቻውን በቂ ኣየይደለም ።መነጋገርያ ጉዳይ(ሃሳብ ) በራሱ በቁምነገር ሚዛ ን የሚነሳ እንዲሆን ያሻል ።ለምሳሌ የማህበራዊ ኑሮ ሁነኛ ገፅታዎችና የሰዎችን የተለያዩ ገጠመኞች የሚያንፀባርቅ ኣንዳች ትምህርት የሚለግስ መሆን አለበት ።ለውይይት የሚውል አርእስት ጉዳይለገዚዘው የመወያያ ውጤት የሚያስገኝ ቢሆንም የኣስተሳሰብ ቢጋርን ተጤይቅን ነገሮችን ግንኙነትና ተዋረድ ለማስተዋል በአግባቡ በመጠቀም የሚያበቃ አይነት ሊሆንይገባል።

ገንቢ ውይይት ለማካሄድ የሚነጋገሩበት ጉዳይ አጣርቶ ከማወቅ ቀጥሎ የሚመጡ ኣያሌ ነገሮች አሉ ።በእነዚህም አንደኛው ፍሬ ነገሩ ባለው ሃሳብ ላይ የሚነጋገር ሰው

የዚያኑ ያህል ጥሩ አድማችነትም ይጠበቅበታል ። ሰጪ ተቀባይም ነው ። ተድያ በሁለቱም በኩል ተባባሪነቱንና ከመነሻው ሊያሳይ ይገባል ።ለጥሩ አድማችነት ሌላ ሀሳብ በጣልቃ ስያስገቡ ቅደምተከተሎችን በሙሉ ልብ መከታተል የንግግሩን ፍሰት አለማቋረጥ ወይም በምን አይነት አለመደናቀፍ የክትትል ጥያቄዎችን ነቃ በሎ መመለስ ወዘተ ያስፈልጋል ።

ምንም ይሁን ምንም በአንዳች አርእስት ነገር ላይ የሚደረግ ክርክር መነሻው መድረሻው የሚያስከትል መሆን አለበት ።ተፈላጊው ማጠንጠኛ ነጥብ ተብለልቶ ሳይወጣ እንዳሁ ልክፍ ቢደረግ በበቂ ማስረጃና ምሳሌ ወይም ሉላ ማሳመኛ መንገድ ሳይደገፍ ቢቀር ውይይቱ ስንኩል ይሆናል ።ዋናውን ሃሳብ ለማጠናከር በማሃል የማነሱ ጉዳዮች ሁሉ ከአርእስት የማይሸሹ ፡መነሻውን የማያዛቡና መድረሻውን የማይተምሙ መሆን ኣለባቸው።

ለመልካም ውይይት ብዙ ነገሮች እንደሚያስፈልጉ የታወቀ ነው፤ዋናዋ ናቸው ከሚባሉት መካከል ለመጥቀስ ከኣሽሙርና ስድብ ከጉራና ትእቢት መቆጠብ አስቀድሞ ኣለመቆጣት ጉዳዮችን ትቶ ሰውየውን በግል አለመቃወም ይገኙበታል ።እነዚህ በተለይ ዲስፕሊን የሚመለከቱ ናቸው ።ጠለቅ ስንል ደግሞ ቃላት መረጣ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ፣ሳያረጋግጡ አለመናገር አንዷን ገፅታብቻ ይዞ የሃሳብ ቋት ልሙላ አለማለት እና ሌሎችም ኣሉ። ከዚህም በላይ የመወያያውን አርእስት አለመለዋወጥ ወይም ከተተለመው መስመር አለመውጣት ፣የተዛባ መእጋቢ ሃሳብ አለማንሳት መሰረታዊ ግንኙነት የሌላቸውንነገሮች አለማምጣት የተገባ ነው።

ክርክር የዚህ ተቃራኒ ሲሆን ውጤቱም እንደዚያው ይሆናል ።ነገር በከንቱ ድካም ብቻ ቢያበቃ ደግ ነው። ግንከዚህ አልፎ ልብ ያውቃል በጣም ልብ ሲያወልቅ ደግሞ ችኮነት ይባላል ።ሌላውን ለማሳመን እውነት ን መንገድ ተከትሎ በአግባቡ ካልተከራከሩ ወይም እኔነትን እያስቀደሙ ሀቁን ኣምነው ካልተቀበሉ ውጤቱ የማይረባ ንትርክ ይሆናል ።

ምንጭ፡-(መስፍን ሀብተማርያም ፣አውደ ኣመት እና ሌሎችም ወገኖች ከገፅ43-54 በማሻሻል)

መመሪያ 1

ከዚህ ቀጥሎ በክርክር ምንነት ዙሪያ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ተገቢ ናቸው ብለህ/ሽ የምታስባቸው/ቢው መልስ ፃፍ/ፃፊ

1. ሰዎች በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ዙርያ ላይ ለምን መወያየት ያስፈልጋቸዋል
2. በአጠቃላይ ሰዎች ለውይይት የሚመርጣቸው ርዕስ ጉዳዮ ምን አይነት መሆን ይኖርባቸዋል
3. ወደ አንድ ክርክር ከመግባትህ/ሽ በፊት ምን ምን ማድረግ ይኖርብሃል/ሻል
4. የጥሩ ተከራካሪ ባህሪያት ከምትላቸው/ከምትያቸው/ አራቱን ፃፍ/ፃፊ/
5. በክርክር ወቅት ከተቃራኒ ቡን የሚያናድድ ሀሳብ ቢስነዘርብህ/ሽ ምን እርምጃ ትወስዳለህ(ጂያለሽ)

መመሪያ 2

ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 1 እስከ 7 የቀረቡትን ጥያቄዎች በቅድሚያ በጥሞና አንብብ/አንብቢ ከዚያም ከጥያቄዎቹ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ካነበብክ/ሽ በኋላ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን በድጋሚ እያነበብክ/ሽ ተገቢውን መልስ ጻፍ/ፊ

1. አንድ የውይይት ተሳታፊ ሰጪም-ተቀባይም ነው ሲል ምን ማለት ነው?
2. ለመልካም ውይይት ከጥሩ የተሳታፊዎች ዲሲፕሊን በተጨማሪ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ሁለቱን ግለጽ/ጪ ?
3. የአንድ ዝርዝር መድረሻና መነሻውን ይዞ የዘለቀ መሆን አለበት ሲባል ምን ማለት ነው?
4. በአንድ ውይይት ላይ የሚሰጥ አስተያየት እንዴት ያለ መሆን አለበት?
5. አንድ የክርክር ሃሳብ ወደ ማይረባ ንትርክ ተለወጠ የሚባለው ምን ሲሆን ነው ?
6. በውይይት ወቅት ከተሳሳተ መዝጋቢ ሐሳብ መነሳት ምንን ያስከትላል?
7. በአንድ ክርክር ላይ ዳኛ ሆነህ ወይም ሆነሽ ብትመረጥ/ጪ ቡድኖቹን የምትገመግምባቸውን አራት ነጥቦች ጻፍ/ፊ

አባሪ 3

የተማሪዎች የንባብ ልምድ እና የአማርኛ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ መደበኛ ልይይት S-D

| Name of school | Reading ability |
|---|---|
| Agulae | 10 |
| Negahs | 24 |
| Wukro | 60 |
| Total | 94 |

**Paired Samples Statistics**

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Reading habit | 62.1383 | 94 | 8.27563 | .85357 |
| | Academic achievement | 56.6064 | 94 | 7.07900 | .73014 |

**Paired Samples Correlations**

| | | N | Correlation | Sig. |
|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | Reading habit& Academic achievement | 94 | .662 | .000 |

**Paired Samples Test**

| | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the Difference | | Me an | Std. Deviation | Std. Error Mean |
| | Lower | Upper | Lower | Upper | Lower | Upper | Lower | Upper |
| Pair 1 Reading comprehension - Academic achievement | 5.53191 | 6.40178 | .66029 | 4.22070 | 6.84313 | 8.378 | 93 | .000 |

አባሪ 4

የተማሪዎች የንባብ ልምድና የአማርኛ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ ስሌት

| | የንባብ ልምድ ውጤት | የአማርኛ ት/ት ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | 67 | 61 |
| 2 | 63 | 54 |
| 3 | 69 | 58 |
| 4 | 53 | 51 |
| 5 | 56 | 56 |
| 6 | 52 | 52 |
| 7 | 68 | 57 |
| 8 | 63 | 50 |
| 9 | 68 | 49 |
| 10 | 48 | 54 |
| 11 | 58 | 58 |
| 12 | 64 | 54 |
| 13 | 67 | 58 |
| 14 | 64 | 52 |
| 15 | 64 | 60 |
| 16 | 65 | 66 |
| 17 | 69 | 60 |
| 18 | 63 | 56 |
| 19 | 57 | 50 |
| 20 | 71 | 63 |
| 21 | 72 | 58 |
| 22 | 68 | 60 |
| 23 | 70 | 63 |
| 24 | 49 | 51 |
| 25 | 67 | 60 |
| 26 | 61 | 51 |
| 27 | 73 | 68 |
| 28 | 57 | 50 |
| 29 | 64 | 57 |
| 30 | 67 | 66 |
| 31 | 70 | 59 |
| 32 | 58 | 49 |
| 33 | 48 | 47 |
| 34 | 65 | 55 |
| 35 | 71 | 60 |
| 36 | 54 | 50 |

| | | |
|---|---|---|
| 37 | 70 | 54 |
| 38 | 63 | 61 |
| 39 | 51 | 53 |
| 40 | 72 | 66 |
| 41 | 67 | 53 |
| 42 | 61 | 56 |
| 43 | 69 | 47 |
| 44 | 54 | 54 |
| 45 | 69 | 57 |
| 46 | 56 | 51 |
| 47 | 68 | 55 |
| 48 | 65 | 60 |
| 49 | 62 | 50 |
| 50 | 59 | 61 |
| 51 | 76 | 56 |
| 52 | 66 | 50 |
| 53 | 74 | 58 |
| 54 | 63 | 52 |
| 55 | 58 | 50 |
| 56 | 40 | 35 |
| 57 | 60 | 60 |
| 58 | 60 | 55 |
| 59 | 68 | 60 |
| 60 | 48 | 50 |
| 61 | 58 | 55 |
| 62 | 64 | 60 |
| 63 | 67 | 65 |
| 64 | 64 | 55 |
| 65 | 65 | 70 |
| 66 | 69 | 70 |
| 67 | 70 | 65 |
| 68 | 60 | 59 |
| 69 | 72 | 70 |
| 70 | 40 | 45 |
| 71 | 70 | 61 |
| 72 | 68 | 47 |
| 73 | 61 | 56 |
| 74 | 57 | 50 |
| 75 | 64 | 60 |
| 76 | 58 | 49 |
| 77 | 48 | 50 |
| 78 | 71 | 75 |
| 79 | 54 | 54 |
| 80 | 63 | 73 |
| 81 | 51 | 50 |

| | | |
|---|---|---|
| 82 | 69 | 57 |
| 83 | 45 | 45 |
| 84 | 73 | 60 |
| 85 | 57 | 61 |
| 86 | 54 | 55 |
| 87 | 65 | 60 |
| 88 | 62 | 61 |
| 89 | 59 | 57 |
| 90 | 60 | 60 |
| 91 | 40 | 45 |
| 92 | 80 | 75 |
| 93 | 70 | 69 |
| 94 | 51 | 50 |

**Case Summaries**

N

| Name of school | Reading ability |
|---|---|
| Agulae | 10 |
| Negahs | 24 |
| Wukro | 60 |
| Total | 94 |

**Correlations (n=94)**

| | | Reading habit | Academic achievement |
|---|---|---|---|
| Reading habit | Pearson Correlation | 1 | .662(**) |
| | Sig. (2-tailed) | . | .000 |
| | N | 94 | 94 |
| Academic achievement | Pearson Correlation | .662(**) | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | . |
| | N | 94 | 94 |

** Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

$r^2 = (0.662)^2 \quad = 0.44$ , That is, 44% of the variation on academic achievement is accounted for the influence of the variation in reading comprehension or the vis versa.

**Descriptive Statistics**

| | Mean | Std. Deviation | N |
|---|---|---|---|
| Reading habit | 61.17 | 12.96 | 94 |
| Reading comprehension | 62.1383 | 8.27563 | 94 |
| Academic achievement | 56.6064 | 7.07900 | 94 |

**Descriptive Statistics**

| | N | Range | Minimum | Maximum | Sum | Mean | Std. Deviation | Variance |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Reading comprehension | 94 | 40.00 | 40.00 | 80.00 | 5841.00 | 62.1383 | 8.27563 | 68.486 |
| Academic achievement | 94 | 40.00 | 35.00 | 75.00 | 5321.00 | 56.6064 | 7.07900 | 50.112 |
| Reading habit | 94 | 60.00 | 15.00 | 95.00 | 5750.00 | 61.1700 | 12.96035 | 33.595 |
| Valid N (listwise) | 94 | | | | | | | |

**Case Summaries**

$r^2 = (0.662)^2 = 0.44$ , That is, 44% of the variation on academic achievement is accounted for the influence of the variation in reading comprehension or the vis versa.

**Descriptive Statistics**

| | Mean | Std. Deviation | N |
|---|---|---|---|
| Reading habit | 61.17 | 12.96 | 94 |
| Reading comprehension | 62.1383 | 8.27563 | 94 |
| Academic achievement | 56.6064 | 7.07900 | 94 |

አባሪ 5

የተማሪዎች ያላቸውን ያንባብ ችሎታና ችሎታቸውን በተግባር ለማዎል ያላቸሁ ብቃት

| ተ.ቁ | ውጤት በመቶኛ | ተ.ቁ | ውጤት በመቶኛ | ተ.ቁ | ውጤት በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 60 | 33 | 47 | 65 | 70 |
| 2 | 54 | 34 | 55 | 66 | 70 |
| 3 | 58 | 35 | 60 | 67 | 65 |
| 4 | 51 | 36 | 58 | 68 | 59 |
| 5 | 56 | 37 | 54 | 69 | 70 |
| 6 | 52 | 38 | 61 | 70 | 45 |
| 7 | 57 | 39 | 53 | 71 | 61 |
| 8 | 50 | 40 | 66 | 72 | 47 |
| 9 | 49 | 41 | 53 | 73 | 56 |
| 10 | 54 | 42 | 56 | 74 | 50 |
| 11 | 58 | 43 | 47 | 75 | 60 |
| 12 | 54 | 44 | 54 | 76 | 49 |
| 13 | 58 | 45 | 57 | 77 | 50 |
| 14 | 52 | 46 | 51 | 78 | 75 |
| 15 | 60 | 47 | 55 | 79 | 54 |
| 16 | 66 | 48 | 60 | 80 | 73 |
| 17 | 60 | 49 | 50 | 81 | 50 |
| 18 | 56 | 50 | 61 | 82 | 57 |
| 19 | 50 | 51 | 56 | 83 | 45 |
| 20 | 63 | 52 | 50 | 84 | 60 |
| 21 | 58 | 53 | 58 | 85 | 61 |
| 22 | 60 | 54 | 52 | 86 | 65 |
| 23 | 63 | 55 | 50 | 87 | 60 |
| 24 | 51 | 56 | 35 | 88 | 61 |
| 25 | 60 | 57 | 60 | 89 | 57 |
| 26 | 51 | 58 | 55 | 90 | 60 |
| 27 | 58 | 59 | 60 | 91 | 45 |
| 28 | 50 | 60 | 50 | 92 | 75 |
| 29 | 57 | 61 | 55 | 93 | 69 |
| 30 | 60 | 62 | 60 | 94 | 50 |
| 31 | 59 | 63 | 65 | | |
| 32 | 49 | 64 | 55 | | |

ለመፈተሽ በተሰጠው ፈተና የተማሪዎች ያገኙት ውጤት በመቶኛ

መስፈርት ከ60 በታች ያገኙ ዝቅተኛ

ከ61-75 ያገኙ መካከለኛ
ከ76-90 ያገኙ ከፍተኛ
ከ91-100ያገኙ በጣም ከፍተኛ
Kavale(1979) እና Nuttal(1982) ያወጡት
መስፈርት።

# አባሪ 6 የቀረበው ሙከራ አስተማማኝነት

(Reliability of the Test)

| Score | F | X |
|---|---|---|
| 1 | 0 | 0 |
| 2 | 0 | 0 |
| 3 | 0 | 0 |
| 4 | 0 | 0 |
| 5 | 0 | 0 |
| 6 | 2 | 12 |
| 7 | 7 | 49 |
| 8 | 3 | 24 |
| 9 | 7 | 63 |
| 10 | 17 | 170 |
| 11 | 10 | 110 |
| 12 | 7 | 84 |
| 13 | 8 | 104 |
| 14 | 7 | 98 |
| 15 | 6 | 90 |
| 16 | 8 | 128 |
| 17 | 6 | 102 |
| 18 | 5 | 90 |
| 19 | 1 | 19 |
| 20 | 0 | 0 |
| | 94 | 1143 |

M = The Mean

Sd = standard deviation

N = No of items in the test

R = Reliability of the test

N = No of student

X = Total grade of student

$M = \frac{ex}{F} = m = \frac{1143}{94} = 12.16$

Sd = Sum of +ag 1/6 score – sum 1/6 both score

Sd =

19+18+18+18+18+18+17+17+17+17+17+17+17+17

+17+6+6+7+7+7+7+7+7+7+8+8+8+9+9+9

½ 94

$Sd = \frac{262-112}{47} = \frac{150}{47} = 3.19$

$R = \frac{y-m-(n-m)}{N(sd)2}$

$R = 1 — \frac{12.16\ (20-12.16}{20\ (3.19)2}$

$R = 1 - \frac{12.16\ (7.84)}{20x\ 10.17}$

$R = 1- \frac{95.33}{203.4}$

R = 1 – 0.46

R = <u>0.54</u>

## አባሪ 7

የተማሪዎች የንባብ ችሎታና ችሎታቸው በተግባር የማዋል ብቃት ለመፈተሽ የቀረበው ፈተና የጥያቄዎች የአስቸጋሪነት መጠን ( Index of item discrimination power (d)

| የጥያቄዎች የአስቸጋሪነት መጠን (p) | | | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ጥያቄውን | በትክክል የሚመልሱ | ጥያቄውን የሚስቱ ተማሪዎች በመቶኛ (p) |
| 1 | 63 | | 67.3 |
| 2 | 30 | | 32.7 |
| 3 | 60 | | 63.6 |
| 4 | 24 | | 25.5 |
| 5 | 46 | | 49.1 |
| 6 | 53 | | 56.4 |
| 7 | 49 | | 52.7 |
| 8 | 49 | | 52.7 |
| 9 | 71 | | 76.4 |
| 10 | 30 | | 32.7 |
| 11 | 85 | | 90.01 |
| 12 | 51 | | 54.5 |
| 13 | 56 | | 59.5 |
| 14 | 46 | | 49.1 |
| 15 | 41 | | 43.6 |
| 16 | 61 | | 64.8 |
| 17 | 40 | | 42.5 |
| 18 | 33 | | 35.1 |
| 19 | 39 | | 41.8 |
| 20 | 30 | | 31.9 |

| የጥያቄዎች የመለየት ብቃት (d) | | | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች | ዝቅተኛ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች | የመለየት ብቃት |
| 1 | 39 | 25 | 0.29 |
| 2 | 23 | 11 | 0.25 |
| 3 | 47 | 27 | 0.44 |
| 4 | 17 | 11 | 0.11 |
| 5 | 41 | 23 | 0.36 |
| 6 | 42 | 22 | 0.44 |
| 7 | 41 | 34 | 0.15 |
| 8 | 35 | 25 | 0.22 |
| 9 | 51 | 37 | 0.29 |
| 10 | 27 | 15 | 0.25 |
| 11 | 59 | 29 | 0.65 |
| 12 | 42 | 25 | 0.36 |
| 13 | 49 | 35 | 0.29 |
| 14 | 34 | 22 | 0.25 |
| 15 | 41 | 32 | 0.18 |
| 16 | 56 | 46 | 0.22 |
| 17 | 35 | 25 | 0.22 |
| 18 | 51 | 37 | 0.29 |
| 19 | 34 | 17 | 0.36 |
| 20 | 52 | 23 | 0.62 |

መስፈርት የ‹ 25 ከሆነ ጥያቄው ከባድ ነው
25‹ የ ‹75 ከሆነ ጥያቄው መካከለኛ ነው
የ› 75 ከሆነ ጥያቄው ቀላል ነው

መስፈርት $d = \frac{\text{correct (T)} - \text{incorrect (E)}}{\frac{1}{2} N}$

N = No of student

$0.39 \geq d \geq 0.20$ ከሆነ የመለየት ብቃቱ ዝቅተኛ ነው።

$D \geq 0.19$ ከሆነ የመለየት ብቃት ከፍተኛ ነው Thorinike,R.M (1997)

መግለጫ

P= Person product movement correlation coefficient

D= Discrimination Power

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑንና በጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሑፎችና መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በሚቀጥለው ስሜንና ፊርማዬን አረጋግጣለሁ።

ስም ብርሃን [illegible] ፊርማ ________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ፣ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

<u>አዲስ አበባ</u>

የካቲት 2003 ዓ.ም.